## መግቢያ፤

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ዋና ኦዲተር መ/ቤት በክልሉ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 116/2 እና መ/ቤቱን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 186/2003 መሠረት፣ በክልሉ የሚገኙ የመንግሥት መ/ቤቶችና ድርጅቶች ለመደበኛ ተግባራትና ለካፒታል ፕሮጀክቶች ማስፈፀሚያ የተመደበላቸውን በጀት በፋይናንስ ሕግ መሠረት ሥራ ላይ ማዋላቸውን፤ የገንዘብና የንብረት አስተዳደራቸው ሕግ፣ደንብና መመሪያን የተከተለ መሆኑን፣ ከምዝበራና ብክነት መጠበቁን ለማረጋገጥ የክልሉን የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ፣ የቆዳ ስፋት፣ የአወቃቀር እርከንና የሴክተር አደረጃጀት፣ ለየመ/ቤቱ እንዲሁም ለመ/ቤታችን የተመደበውን በጀት፣ ያለውን የሰው ኃይል እና ሌሎች ተጨባጭ ሁኔታዎችን ከግንዛቤ በማስገባት አጠቃላይ ተቀባይነት ያላቸውን የኦዲት ደረጃዎችና የአሠራር ሥርዓቶችን በመከተል ያከናወናቸውን ተግባራት ያካተተ አጠቃላይ ዘገባ በዚህ ጥራዝ ቀርቧል፡፡ በዚህ መሠረት የተጠቃለለው ውጤት እንደሚያመለክተው፡-

1. መ/ቤቱ ከጥር 2008 እስከ የጥር 30/2009 ዓ/ም ባሉት ወራት የ288 መ/ቤቶችን የ2008 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ለማድረግ አቅዶ የ268 (93%) ተከናውኗል፡፡ የሁሉም መ/ቤቶች ኦዲት ውጤት በዚህ ሪፖርት ተጠናቅሮ ቀርቧል፡፡
2. የ2008 በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት የተደረገ መ/ቤቶች በአወቃቀር እርከን ሲታይ በክልል/ማእከል 73(27%)፣በዞን 11(4%)፤በከተማ አስተዳደሮች 41(15%) ቀሪዎች 143(54%)፤በወረዳ ደረጃ ያሉ ናቸው፡፡ በአጠቃላይ የ2008 በጀት ዓመት ሂሳብ የኦዲት ሽፋን በአሁኑ ጊዜ ካሉት 442 ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ቁጥር አንፃር ሲታይ 60.63% የደረሰ ሲሆን የኦዲት ሽፋኑ ከበጀት አንጻር ሲታይ ደግሞ አጠቃላይ ኦዲት የተደረገ መ/ቤቶች የበጀት ወጪ ብር 23,498,976,462.20 በመሆኑ ለ2008 በጀት ዓመት በክልሉ ምክር ቤት ከታወጀው ብር 27,297,881,286.00 አኳያ ሲታይ 86% የኦዲት ሽፋን ላይ እንደተደረሰ መረጃው ያሳያል፡፡
3. ለኦዲቱ መሠረት የሆኑት ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ያቀረቧቸው የሂሣብ መዛግብትና ሰነዶች፣ የሂሳብ መግለጫዎች እንዲሁም በየደረጃው ያሉ የሚመለከታቸው ኃላፊዎች የሠጧቸው ማብራሪያዎች ናቸው:: ከዚህም በተጨማሪ ከ3ኛ ወገን የተገኙ ብቃትና ተቀባይነት ያላቸው ማስረጃዎች ሥራ ላይ ውለዋል::
4. የመ/ቤቶቹን ሂሳብ ኦዲት ማድረግ የመ/ቤታችን ኃላፊነት ሲሆን የሂሣብ መግለጫዎች የማዘጋጀት፣ ኦዲት የማስደረግና የሠሩበትን ሁኔታ የማስረዳት እንዲሁም በኦዲት ግኝቶች ላይ የማሻሻያ እርምጃ መውሰድ የኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ኃላፊነት ነው::
5. የኦዲቱ ዋና ዋና ግኝቶች ከጥሬ ገንዘብ፣ከገቢ፣ከተሰብሳቢ፣ከወጪ፤ከተከፋይ፣ከበጀት፣ከሂሣብ ሪፖርቶችና ከንብረት አስተዳደር ኦዲት የተገኙ ሲሆኑ በዚህ ሪፖርት በዝርዝር ቀርበዋል፡፡
   በበጀት ዓመቱ በድምሩ ብር 6,038,504.24 የገንዘብ ጉድለትና ማጭበርበር የተከሰተ እንዲሁም ለግል ጥቅም የዋለ ሲሆን ከዚህ ዉስጥ ከፍተኛ ድርሻ የያዙት መ/ቤቶች እንደሚከተለው ተዘርዝረዋል፡፡

- ስማዳ ወረዳ ገቢዎች ጽ/ቤት ብር 2,977,097.94፣ደብር ብርሀን ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ብር 357,752.44፣ ሜጫ ወረዳ ጤና ጥበቃ እና ግብርና ጽ/ቤት ብር 311,572.00፣ አንዳሳ ዶሮ ብዜት ማዕከል ብር 283,052.99፣መተማ አብርሃ ጅራ ሁር ኡመር መንገድ ስራ ፕሮጀክት ብር 278,237.38 ፣ምስራቅ አማራ ውሃ ስራዎች ድርጅት ብር 274,235.82፣ቆቦ ከተማ አስተዳደር አገልግሎት ጽ/ቤት ብር 189,662.06፣ ዓንን ወረዳ ገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር

ጽ/ቤት ብር 186,976.10፣በረና ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 115,913.53፣ደባርቅ ከተማ አስ/ገ/ኢ/ል/ጽ/ቤት ብር 104,062.01፣ ጎንጅ ቆለላ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 101,341.89፣ ኮምቦልቻ ደሮ ብዛት ማዕከል ብር 96,849.76፣ ምዕራብ በለሳ ወረዳ ግብርና ጽ/ቤት 85,164.63፣የመሀል ሳይንት ወረዳ ደንሳ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት ብር 73,370.88፣ ይስማላ ጤና አጠባበቅ ጣቢያ ብር 72,147.39 ፣ወገራ ወረዳ ጤና ጥበቃ ጽ/ቤት ብር 54,054.75፣ክልል ምክር ቤት ብር 49,772.30፣እንፍራንዝ ከተማ ንዑስ መዘጋጃ ቤት ብር 41,705.78፣ ተሁለደሬ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 40,250.66፣ግሸራቤል ወረዳ ውሃ ሀብት ልማት ጽ/ቤት ብር 39,585.19 ፣አዊ ብሄረሰብ ዞን ጤና መምሪያ ብር 35,972.37 ፣ግዳን ወ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 29,209.66 ፣ፎገራ ወረዳ ገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ጽ/ቤት ብር 26,669.24፣ዳንግላ ወረዳ ጊሣ ንዑስ ማዘጋጃ ቤት ብር 22,208.21፣አዲስ ፋና አጠ/1ኛ ደ/ት/ቤት ብር 19,428.07፣ አነደድ ወረዳ ዳገት ት/ቤት ብር 18,272.00፣የምስራቅ በለሳ ከተማ ጉሃላ ንፁህ መጠጥ ውሃ አቅርቦት ብር 13,736.50፣መተማ ወረዳ ኮኪት 1ኛ/ደ/ት/ቤት 12,110.00 እና ደላንታ ወረዳ ገቢዎች ጽ/ቤት ብር 11,187.36 ሲሆኑ ከላይ የተጠቀሱት የመንግስት መ/ቤቶች ከብር **10,000.00** በላይ ጉድለት/ማጭበርበር በመፈጸም ከፍተኛውን ድርሻ የያዙ ናቸው፡፡

6. በዚህ አጠቃላይ ዘገባ ለየመ/ቤቱ ከተላከው የፋይናንስና ህጋዊነት ኦዲት ሪፖርቶች ዝርዝር ተለቅመው የተጠቃለሉ ግኝቶች እንዲሁም ከ2004 እስከ 2008 ባሉት 5 ዓመታት በተከናወነ ኦዲትና በተዘጋጁት የኦዲት ሪፖርቶች መሠረት አዝማሚያውን ለማሳየት የዋና ዋና ግኝቶች አማካይ ውጤት በግራፍ ተደግፎ ቀርቧል፡፡ የዚህ ሪፖርት ዋና ዓላማ የክልሉ ምክር ቤት የበጀትና መንግስት ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፣ የርዕሰ መስተዳድር ጽ/ቤትና ሌሎችም የሚመለከታቸው አካላት ኦዲት የተደረጉ መ/ቤቶችን ግኝቶች በመገምገም የፋይናንስ፣ ግዥና ንብረት አስተዳደሩን አጠቃላይ ሁኔታዎች ለማሻሻል ለሚደረጉ ውሳኔዎች እንዲጠቀሙብትና ተጠያቂነትንም ለማጠናከር በማሰብ የቀረበ ነው፡፡
7. የሪፖርቱ አቀራረብ የ2008 በጀት ዓመት ሂሣብ የፋይናንስና ህጋዊነት ኦዲት ውጤት፣ያለፉት አምስት ዓመታት አፈጻጸም አዝማሚያ ትንተና ማጠቃለያና የማሻሻያ አስተያየት በቅደም ተከተል ከምዕራፍ 1-3 በማካተት ሲሆን ለሪፖርቱ ደጋፊ አባሪዎች -------ገጽ በሪፖርቱ መጨረሻ ተያይዘዋል፡፡

## ምዕራፍ -አንድ

1. የፋይናንስና ህጋዊነት ኦዲት ዕቅድ አፈፃፀም፣

### 1.1. የኦዲት ሽፋን፣

#### 1.1.1. የኦዲት ሽፋን በክልል/ማዕከል፣ከተማ እና በዞን □ረጃ፣

በበጀት ዓመቱ ኦዲት የተደረጉ መ/ቤቶች በክልል/ማዕከል እና በዞን □ረጃ የተያዘው ዕቅድና አፈፃፀም በንጽጽር ከዚህ ቀጥ ሎ ቀርቧል፡፡

ሠንጠረዥ -1 የኦዲት ሽፋን በክልል/ማዕከል፣ከተማ እና ዞኖች ከ2007 ክንዉን ጋር በንፅፅር

| ተ.ቁ | ዞናዊ ሥርጭት | የ2007 | የ2008 | | ንጽጽር | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ክንውን | ዕቅድ | ክንውን | ከዓመቱ ዕቅድ% | የ2008 ከ2007 ክንውን% |
| | | ብዛት | ብዛት | ብዛት | | |
| 1 | □□ልል /ማዕከል / መ/ቤቶች | **70** | **78** | **73** | **25** | **4.28** |
| 2 | ባህር ዳር ከተማ አስተዳደር | **1** | **2** | **2** | **1** | **100** |
| 3 | ምዕራብ ጎጃም | **16** | **25** | **24** | 8 | **50** |
| 4 | ምስራቅ ጎጃም | **25** | **25** | **24** | 8 | **-4** |
| 5 | ሰሜን ጎንደር | **20** | **18** | **17** | 6 | **-15** |
| 6 | ደቡብ ጎንደር | **16** | **20** | **19** | 7 | **18.75** |
| 7 | አዊ ብሔ/አስተዳደር | **12** | **16** | **15** | 5 | **25** |
| 8 | ሰሜን ወሎ | **17** | **17** | **15** | 5 | **-11.76** |
| 9 | ደቡብ ወሎ | **28** | **35** | **32** | 11 | **14.28** |
| 10 | ሰሜን ሸዋ | **28** | **32** | **29** | 11 | **3.57** |
| 11 | ዋግኽምራ ብሔ/ አስተዳደር | **8** | **10** | **9** | 3 | **12.5** |
| 12 | ኦሮሞ ብሔ/አስተደደር | **8** | **10** | **9** | 3 | **12.5** |
| | ድምር | **249** | **288** | **268** | **93** | **7.63** |

**ማሳሰቢ□፣**

- የ2008 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ክንውን ካለፈው ዓመት ጋር ሲነፃፀር ልዩነቱ የጨመረበት ምክንያት በጀት ዓመቱ የኦዲት ሽፋንን ለማሳደግ በተሰጡ ስልጠናዎች ምክንያት የመፈፀም አቅም ማደግ በመቻሉ ነው፡፡

#### 1.1.2. የኦዲት ሽፋን በአወቃቀር እርከን፤

**የ2008** በጀት ዓመት ዕቅድ ክንውን በአወቃቀር□እርከን□ሲ.ታ□ እንደሚከተለው ነው፡፡

ሠንጠረዥ 2. የኦዲት ሽፋን በአወቃቀር□እርከን

| ተ.ቁ | የአወቃቀር እርከን | 2008 ሂሣብ ኦዲት ክንውን | |
|---|---|---|---|
| | | በመ/ቤት ብዛት | ከጠቅላላዉ ክንዉን በ% |
| **1.** | □ልል/ማዕከል | 73 | 27 |
| **2.** | ዞን አስተዳ□ር | **11** | **4** |
| **3.** | □ረ□ | **143** | **54** |
| **4.** | ከተማ አስተ□□ር | **41** | **15** |
| **ትምር** | | **268** | **100** |

### 1.2 የኦዲት ስልት:-

የ2008 በጀት ዓመት ሂሳባቸው ከጥር 1/2008 እስከ የካቲት 30/09 በጀት ዓመት ኦዲት ከተደረጉት 268 መ/ቤቶች ውስጥ 221 (82.47%) በንሞና እንዲሁም 47(17.53%) መ/ቤቶች የልዩ ኦዲት ጥቆማና ጥያቄ ቀርቦባቸው በየነጥቦቹ መነሻ መሠረት በዝርዝር ኦዲት የተደረጉ ናቸዉ::

የኦዲት ሥራውን በአብዛኛ□ በመ□በኛ□ በንሞና የኦዲት ስልት ለማከናወን ታቅዶ 82.47% በንሞና የኦዲት ዘዴ ኦዲት የተደረገ ሲሆን የኦዲት ሥልቱ □ለም አቀፍ ተቀባይነትን ያገኘና በዝርዝር ኦዲት ተደርጎ ከሚገኝ□ ጥቅም ያላነሰ ውጤት ሊያስገኝ የሚያስችል ዘመናዊና በተመጣጣኝ □ስ□□ን□ልና ወጪ ሥራውን ለማከናወን ጊዜና ገንዘብ ቆ□ቢ መሆኑ የተመረጠ እና በሃብት አስተዳደርና አጠቃቀም ዙሪያ ስጋት ያለበትን አካባቢ ትኩረት ስለሚሰጥ አዋጭ በመሆኑ ነው::

የንሞና ኦዲት ስልትን አስመልክቶ ካለፈዉ በጀት ዓመት አፈፃፀም የዕቅድ ክንውን በንጽጽር □እንደሚከተለ□ ቀርቧል::

ሠንጠረዥ 3. የኦዲት ስልት፤

| ተ.ቁ. | የኦዲት ስልት | 2007 ሂሣብ | | 2008 ሂሣብ | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | ክንውን ብዛት | % | ክንውን | % |
| 1 | ንሞና | **206** | 82.73 | **221** | 82.47 |
| 2 | ል□ ኦዲት | 43 | 17.27 | 47 | 17.53 |
| | **ትምር** | **249** | **100** | **268** | **100** |

በንሞና የኦዲት ዘዴ ኦዲት የተደረጉ መ/ቤቶች የ2008 ክንውን (82.47%) መሸፈኑ የሚያሣየው የኦዲት አፈፃፀሙ ዘመናዊና ወጪ ቆጣቢ አሠራር የተከተለ መሆኑን ሲሆን በዝርዝር እንዲሠሩ የቀረቡና ኦዲት የተደረጉ የልዩ ኦዲት ጥያቄዎች 47 መ/ቤቶች /17.53%/ መሆናቸውን ያመለክታል።

### 1.3. <u>የኦዲት አስተያየቶች</u>፣

የ2008 በጀት ዓመት ሂሳባቸው ኦዲት ተደርጎ ወጪ የሆኑ ሪፖርቶች 268 ሲሆኑ የተሰጠው የኦዲት አስተያየት ከ2007 በጀት ዓመት ሂሳብ ጋር ተነፃፅሮ እንደሚከተለው ከዚህ ቀጥሎ ተመልክቷል፤

ሠንጠረዥ 4 የኦዲት አስተያየቶች፣

| ተ.ቁ | የኦዲት አስተያየት | የ2007 ሂሣብ | | 2008 ሂሣብ | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | የመ/ቤት ብዛት | በ% | የመ/ቤት ብዛት | በ% |
| 1 | አስተያየት መስጠት አለመቻል | 5 | 2 | 3 | 1 |
| 2 | አጥጋቢ አይደለም | - | - | 3 | 1 |
| 3 | ከዚህ በስተቀር | 196 | 78.72 | 203 | 76 |
| 4 | ንፁህ | 5 | 2 | 6 | 2 |
| 5 | አስተያየት ያልተሰጠው | - | - | 6 | 2 |
| 6 | ልዩ ኦዲት | 43 | 17.28 | 47 | 18 |
| | **ድምር** | 249 | 100 | 268 | 100 |

ከሰንጠረዡ እንደምንረዳው የ2008 በጀት ዓመት ሂሣባቸው በመደበኛው ኦዲት ከተ□ረጉ 268 መ/ቤቶች ውስጥ ለ203 (76%) ከዚህ በስተቀር፣ ለ3 (1%) አስተያየት መስጠት አልተቻለም፣ ለ3 (1%) አጥጋቢ አይደለምም፤ ለ6 (2%) ንፁህ አስተያየት፣ለ6(2%) በተለያየ ምክንያት በከፊል የተሰሩ ሲሆኑ አስተያየት ያልተሰጣቸው እና 47(18%) የልዩ ኦዲት ሥራ በመሆናቸው የኦዲት አስተያየት የማይጠበቅባቸው ናቸው፡፡

በ2008 በጀት ዓመት ኦዲት ተደረጎ የተሰጠዉ የኦዲት አስተያየት በ2007 በጀት ዓመት ከተሰጠው የኦዲት አስተያየት ጋር ሲነጻጸር " **ንፁህ አስተያየት የሚለው"** በ20% መጨመሩ፣ **"አስተያየት መስጠት አለመቻል"** በ40% መቀነሱ የሂሣብ አያያዝ ስርዓቱ መሻሻል ማሳየቱን የሚያመላክት ሲሆን አስተያየት የማይሰጥበት የልዩ ኦዲት ሂሣብ ደግሞ በ9.30% መጨመሩ ደግሞ ህብረተሰቡ የኪራይ ሰብሳቢነት አመለካከትና ተግባር የመታገል ልምዱ እየጨመረ መሄዱን ያሳያል፡፡ በሌላ በኩል **"አጥጋቢ አይደለም"** የሚለው መጨመሩ ችግሮች እንዳሉ መረዳት ያስችላል::

## የኦዲት አስተያየቶች መገለጫዎች፤

1. **"አጥጋቢ አስተያየት"**የሚሰጠው ይህ ነው የሚባል ግኝትና የአሰራር ችግር ያልተገኘበት መ/ቤት ነው፡፡
2. **"ከዚህ በስተቀር"** የሚል አስተያየት የተሰጠባቸው የኦዲት ሪፖርቶች ከተወሰኑ ግኝቶችና የአሠራር ችግሮች በስተቀር የተሻለ አፈፃፀም የሚታይባቸው ናቸው::
3. **"አጥጋቢ አይደለም"** □ሚል አስተያየት የተሰጠባቸው መ/ቤቶች መንግሥት የመደበላቸውን ሀብት /ገንዘብ/ በአግባቡና ህጉ በሚፈቅደው አሰራር መሠረት ስራ ላይ ያላዋሉ፤የማጭበርበር ተንኮል የተፈፀመባቸው፤ ጉልህና መሠረታዊ ግኝቶችና የአሰራር ችግሮች የተስተዋሉባቸው ናቸው፡፡
4. " **አስተያየት መስጠት አልተቻለም**" የሚል አስተያየት የተሰጠባቸው መ/ቤቶች ደግሞ መንግሥት የመደበላቸውን ሀብት እንዴት ሥራ ላይ□እንዳዋሉት የሚገልፅ የተሟላ ማስረጃ ያልቀረበባቸው፣ □□ስዓ ቁዓ ዓ ር ሥር□ታቸው በጣም የተዳከመ በመሆኑ የሂሳቡን ትክክለኛነት በኦዲት ለማረጋገጥ ያልተቻለባቸው ናቸው፡፡

በአጠቃላይ በተራ ቁጥር-3 እና 4 የተገለጹት አስተያየቶች የተሰጡባቸው መ/ቤቶች ግኝቶቻቸውና የአሰራር ችግሮቻቸው ጉልህና መሠረታዊ የሆኑባቸው መ/ቤቶች ናቸው::

ስለሆነም የሚመለከታቸው ሁሉ በሪፖርቶቹ የቀረቡ ችግሮች ጉልህና መሠረታዊ መሆናቸውን በመገንዘብ አስፈላጊውን የማስተካከያ እርምጃ መ□ሰት □ቷበቅባቸዋል፡፡

## 1.3.1 "አስተያየት መስጠት አልተቻለም" የሚል የኦዲት አስተያየት የተሰጠባቸው መ/ቤቶች፤

የ2008 በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት ከተደረጉት 268 መ/ቤቶች ውስጥ 3(1%) መ/ቤቶች የገንዘብ አያያዝና አስተዳደሩም ሆነ የዉስጥ ቁጥጥር ሥርዓቱን መርምሮ ተዓማኒና በቂ የሂሳብ አያያዝና አስተዳደር መኖሩን ለማረጋገጥና ስለ ሂሳቡ ትክክለኛ መሆን አለመሆን የሙያ አስተያየት ለመስጠት ባለመቻሉ ይህም ጉልህና መሰረታዊ ችግር በመሆኑ ‹‹**አስተያየት መስጠት አልተቻለም**›› የሚል የኦዲት አስተያየት ተሰጥቷል፡፡ይህ የኦዲት አስተያየት የተሰጠባቸው መ/ቤቶች ዝርዝር እና ለአስተያዩቱ ዋና ዋና ምክንያቶች ከዚህ እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

#### 1.3.1.1. ላይ ጋይንት ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰጭ/ማዕከል

- ከተፈጥሮ ሚዛኑ ውጪ የተመዘገበ እና በሪፖርትም የተመላከተ የባንክ ሂሳብ ብር 1,954,980.00፣
- ለኦዲት ስራ ያልቀረበ ብዛት 144 ጥራዝ ደረሰኞች በገንዘብ መጠናቸው ብር 27,175.00፣
- ኦዲት ማድረግ ያልተቻለ የማሽነሪ ኪራይ ክፍያብር 3,185,822.14
- የሂሳብ መቆጣጠሪያ ሌጀር ካርድ ያልተቋቋመለት የትምህርት ጥራት ሂሳብ መኖሩ፣
- የንብረት ሂሳብ መዛግብት እና ቆጠራ የተሟላ ባለመሆኑ ንብረትን ኦዲት ማድረግ አለመቻሉ፣

#### 1.3.1.2. ሜጫ ወ/ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል

- የጥሬ ገንዘብ ሂሳብን ኦዲት ማድረግ አለመቻሉ፣
- ለመደበኛ ሂሳብ ጂ.ኦ.ቪ. 1000062627844 የባንክ ሂሳብ ማስታረቂያ ያልተዘጋጀለት መሆኑ፣
- የስፖርት ምክር ቤት ገቢ ሂሳብን ኦዲት ማድረግ አለመቻሉ፣
- ያለአግባብ የተከፈለ የውሎ አበል ብር 26,311.80፣
- በተጭበረበረ መንገድ የተከፈለ የስልጠና አበል ብር 298,940.00፣
- ለስፖርት ምክር ቤት ሂሳብ ሪፖርት ያልተዘጋጀ መሆኑ፣
- የንብረት ሂሳብ ኦዲት ማድረግ አለመቻሉ፣

#### 1.3.1.3 ታች ጋይንት ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰጭ/ማዕከል

- ለኦዲት ስራ ያልቀረቡ ብዛት 2 ጥራዝ እና 42 ቅጠል የመደበኛ ገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኝ ብር 17,537.43፣
- ለኦዲት ስራ ያልቀረቡ ብዛት 53 ጥራዝ እና 11 ቅጠል የስፖርት መክር ቤት ገቢ
  መሰብሰቢያ ደረሰኝ ብር 59,910.00፣ የስፖርት የገቢ ሂሳብ ማጠቃለያ ደረሰኝ ብር 263,300.48፣
- የእንስሳት ጤና አገልግሎት ገቢ ሂሳብን ኦዲት ማድረግ አለመቻሉ፣መገኘቱ ተረጋግጧል፡፡

### 1.3.2. "አጥጋቢ አይደለም" የሚል የኦዲት አስተያየት የተሰጠባቸው መ/ቤቶች፤

የ2008 በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት ከተደረጉት 268 መ/ቤቶች ውስጥ 3(1%) መ/ቤቶች የገንዘብ አያያዝና አስተዳደሩም ሆነ የዉስጥ ቁጥጥር ሥርዓቱ አጥጋቢ ሆኖ ባለመገኘቱ ይህም ጉልህና መሰረታዊ ችግር በመሆኑ "አጥጋቢ አይደለም"›› የሚል የኦዲት አስተያየት ተሰጥቷል፡፡ይህ የኦዲት አስተያየት የተሰጠባቸው መ/ቤቶች ዝርዝር እና ለአስተያዩቱ መነሻ ምክንያቶች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

#### 1.3.2.1. እንሳሮ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል

- ህጋዊ ባልሆነ ደረሰኝ የፀደቀ ወጭ ብር 5618.70፣
- በብልጫ የፀደቀ ወጭ ብር 24391.25፣
- አላግባብ የተከፈለ የትምህርት ፌስቲቫል ሂሳብ ብር 30,000.00፣
- በመደበኛ በጀት የወጭ ሂሳብ ሌጀር ሳይዘጋጅ የተከፈለ ብር 50,496,913.04፣
- የተከፋይ ሂሳብን ኦዲት ማድረግ አለመቻሉ፣ መገኘቱ፣

#### 1.3.2.2. ሸዋሮቢት ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል

- የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ኦዲት ማድረግ አለመቻሉ፣
- ለመናህሪያ አገልግሎት ገቢ ሂሳብ የባንክ አካውንት አለመከፈቱ፣
- ያልተሰበሰበ የቅጣት ገቢ ብር 472,821.60፣

- መሰብሰብ ሲገባው ያልተሰበሰበ የስራ ግብር ብር 25,777.45፣
- ኢኮኖሚያዊ ባልሆነ መንገድ የተፈፀመ ግዥ ብር 20,997.00፣
- ህጋዊ ደረሰኝ ሳይቀርብ የተፈፀመ ክፍያ ብር 19,150.00፣
- አላግባብ የተከፈለ ውሎ አበል ብር 81,278.15፣

#### 1.3.2.3. ወልድያ ሆስፒታል

- የባንክ ሂሳብ ትክክለኛነት ማረጋገጥ አለመቻሉ
- የፋርማሲ የመድሀኒት ሽያጭ ገቢን ኦዲት ማድረግ አለመቻል፣
- በወቅቱ ያልተሰበሰበ የተሰብሳቢ ሂሳብ ብር 420,5570.54፣
- ኢኮኖሚያዊ ባልሆነ መንገድ የተፈፀመ ግዥ ብር 15,200.00፣
- አላግባብ የተከፈለ የስልጠና አበል ብር 15,356.00፣
- በወቅቱ ያልተከፈለ የተከፋይ ሂሳብ ብር 4,994,713.08፣ መገኘቱ፡፡

## 1.4. መልስ ያልሰጡ መ/ቤቶች፣

ይህ ሪፖርት እስከተጠቃለለበት ሰኔ 23/2009 ዓ/ም ድረስ መልስ ያልሰጡ መ/ቤቶች ዝርዝር እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

**የክልል /ማዕከል/ መ/ቤቶች**

1. ሰቆጣ ማረሚያ ቤት
2. በጌምድር መምህራን ትምህርት ኮሌጅ

**ምዕራብ ጎጃም ዞን አስተዳዳር**

3. ወንበርማ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል
4. ሰሜን አቸፈር ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል

**ምስራቅ ጎጃም ዞን አስተዳዳር**

5. ስናን ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል

**ሰሜን ጎንደር ዞን አስተዳደር**

6. መተማ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል

**ደቡብ ወሎ ዞን አስተዳዳር**

7. ቦረና ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል
8. ከለላ ወረዳ ነ/ፋድ/ስ/ማዕከል
9. ወረኢሉ ወረዳ ነ/ፋድ/ስ/ማዕከል
10. መቅደላ ወረዳ ነ/ፋድ/ስ/ማዕከል
11. መሀል ሳይንት ነ/ፋድ/ስ/ማዕከል
12. ወረባቦ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል

**ሰሜን ወሎ ዞን አስተዳደር**

13. ቡግና ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል

**ሰሜን ሸዋ ዞን አስተዳደር**

14. መራ ቤቴ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል
15. መሀል ሜዳ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል

**ደቡብ ጎንደር ዞን አስተዳደር**

16. ደብረ ታቦር ከተማ አስ/ገቢዎች ጽ/ቤት
17. ታች ጋይት ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል
18. ሊቦ ከምከም ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል

**አዊ ብሄረሰብ አስተዳደር**

19. አንከሻ ጓጉሳ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል
20. ዳንግላ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል

**ዋግኽምራ ብሔረሰብ አስተዳደር**

21. ዳህና ወረዳ ነ/ፋድ/ስ/ማዕከል
22. ዝቋላ ወረዳ ነ/ፋድ/ስ/ማዕከል

በአጠቃላይ መልስ አሰጣጡ ባለፈው ዓመት ተመሳሳይ ጊዜ በመደበኛ ኦዲት ከተደረጉ 206 መ/ቤቶች 23(11.16%) መልስ ካልሰጡ መ/ቤቶች ጋር ሲነጻጸር በበጀት ዓመቱ በመደበኛ ኦዲት ከተደረጉት 221 መ/ቤቶች መልስ ያልሰጡት 22(9.95%) ስለሆኑ የዚህ ዓመት መልስ አሰጣጥ ካለፈዉ በጀት ዓመት ጋር ሲነፃፀር መሻሻል የታየበትና የተጠያቂነት ሥርዓትን ለማረጋገጥ መ/ቤታችን ከሚመለከታቸው ተቋማት ጋር በፋይናንስ ግልፀንነትና ተጠያቂነት ዙሪያ እየሰራ ያለው ስራ ውጤት መሆኑን የሚያመላክት ሲሆን በልዩ ኦዲት ከተሰሩት 47 መ/ቤቶች ውስጥ ደግሞ እርምጃ ያልተወሰደባቸው 33 (70.2%)መሆናቸው እርምጃ የመውሰድ ሂደቱ አዝጋሚ ሆኖ ይታያል፡፡

## 1.5 የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ኦዲት ውጤት፤

### 1.5.1. □ዓ ሬ ገንዘብ ሂሳብ ጉድለትና ብል□ ፣

ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች የጥሬ ገንዘብ ሂሣብ በየጊዜው ቁጥጥር እያደረጉ መያዝ ይጠበቅባቸዋል፡፡ በዋና ኦዲተር መ/ቤት በኩል የበጀት ዓመቱን የጥሬ ገንዘብ ሂሳብን የማረጋገጥ ተግባር ትኩረት ተደርጎ እየተሠራ ያለ ተግባር ነው፡፡ በተጨማሪም በአንዳንድ የኦዲት ሥራዎች ላይ ሁኔታዎች ትኩረት ሲስቡና የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ እንዲረጋገጥ በልዩ ሁኔታ የሚቀርቡ ጥያቄዎችን በወቅቱ በመቀበል የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ የማመዛዘን ተግባር የሚከናወን ሲሆን የኦዲት ውጤቱ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡ ሠንጠረዥ 5 የጥሬ ገንዘብ ጉድለትና ብልጫ፣

| ተ.ቁ | ኦዲት ተደራጊው ማዕከል ዞን | ጉድለት | | | ትምር | የገንዘብ □ዬ ብል□ | የሌጀር ከወጪ ቀሪ ከቆጠራ ልዩነት | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | የመ/ቤት ብዛት | ከአሁን ገንዘብ □ዬ | ከቀድሞ ገንዘብ ያዥ | | | በመብለጥ | በማነስ |
| 1 | ክልል/ ማዕከል | 2 | 33,555.39 | | 33,555.39 | | | |
| 2 | ባህር ዳር ከተማ | - | - | | | | | |
| 3 | ምክ/ጐጾም | 1 | 72,147.39 | | 72,147.39 | | | |
| 4 | ምስራቅ ጎጃም | 1 | 6,800.00 | | 6,800.00 | | 49,273.84 | |
| 5 | ሰሜን ጐንደር | 2 | 117,798.51 | | 117,798.51 | | 150,910.55 | |
| 6 | ደቡብ ጎንደር | | | | | | 237,657.72 | |
| 7 | የአዊ ብሔ/አስተ/ | 1 | 22,208.21 | | 22,208.21 | | 523,966.99 | |
| 8 | ሰሜን ወሎ | 1 | | 29,209.66 | 29,209.66 | | 1,651,001.75 | |
| 9 | □ቡብ ወሎ | 5 | | 385,550.66 | 385,550.66 | | 1,950,836.95 | 1,352,042.31 |
| 10 | ሰሜን ሸዋ | - | | | | | 172,234.61 | |
| 11 | ኦሮሞ ብሔ/አስተ/ | - | | | | | | |
| 12 | ዋግኽምራ ብሔ/አ | - | | | | | | |
| ትምር | | 13 | 252,509.50 | 414,760.32 | 667,269.82 | | 4,735,882.41 | 1,352,042.31 |

የ2008 በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት ከተደረጉ መ/ቤቶች በድምሩ ብር 667,269.82 ጉድለት የተገኘ ሲሆን ከዚህ ውስጥ ከቀትሞ ገንዘብ ያዡች ብር 414,760.32 በጉድለት ተገኝቷል፡፡

እንዲሁም በበጀት ዓመቱ መጨረሻ (ሰኔ 30) በጥሬ ገንዘብ ከወጪ ቀሪ መከታተያ ሌጀር መሠረት መገኘት ያለበት እና በካዝና ተገኝቶ የተቆጠረ የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ሲነጻጸር በ15 መ/ቤት ብር 4,735,882.41 የተቆጠረ ገንዘብ ከሌጀር ከወጪ ቀሪ በማነስ እና በ2 መ/ቤት ቆጠራ ከሌጀር ከወጪ ቀሪ በመብለጥ ብር 1,352,042.31 ተስተውሏል፡፡ ዝርዝሩን (አባሪ 2 ይመልከቱ፡፡)

- ✓ **የጥሬ ገንዘብ ጉድለት የታየባቸው መ/ቤቶች** አንዳሳ ዶሮ ብዜት ማዕከል ብር 29,417.72 የእለት ገንዘብ ሰብሳቢው ከ05/11/03 እስከ 17/02/08 ዓ.ም ድረስ ያንቀሳቀሰው የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ተመዛዝኖ የተገኘ ጉድለት፣ የይስማላ ጤና አጠባበቅ ጣቢያ ብር 72,147.39 የፋርማሲ ባለሙያው ከ23/11/2000 እስከ 14/6/2005 ዓ.ም ድረስ ስራቸውን ሲያከናውኑ ለታካሚዎች በሽያጭ የቀረበ እና ለነፃ ታካሚዎች በነፃ እንዲሰራጭ በእርዳታ የተገኘ መድሃኒት በመሸጥ ለግላቸው በመጠቀም የተገኘ የጥሬ ገንዘብ ጉድለት፣ ደባርቅ ከተማ አስ/ገ/ኢ/ል/ጽ/ቤት ብር 104,062.01 የዕለት ገንዘብ ሰብሳቢው ከ01/04/06 እስከ 15/10/08 ዓ.ም ድረስ በየዕለቱ የተሰበሰበው ከመናኸሪያ አገልግሎት እና ከንግድ ፈቃድ እድሳት ገቢ የሰበሰበው ጥሬ ገንዘብ ተመዛዝኖ የተገኘ ጉድለት፣ የምስራቅ በለሳ ከተማ ጉሃላ ንፁህ መጠጥ ውሃ አቅርቦት ብር 13,736.50 ዋና ገንዘብ ያዥ ስራ ከጀመሩበት ከ01/02/2003 እስከ 30/10/06 ዓ.ም ድረስ ያንቀሳቀሱት የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ተመዛዝኖ የተገኘ የጥሬ ገንዘብ ጉድለት፣ዳንግላ ወረዳ ጊግ ንዑስ ማዘጋጃ ቤት ብር 22,208.21 ከ17/03/06 እስከ 08/04/2008 ዓ.ም ድረስ የእለት ገንዘብ ሰብሳቢው የሰበሰቡትን የመንግስት ገቢ ፈሰስ ባለማድረጋቸው ተመዛዝኖ የተገኘ የጥሬ ገንዘብ ጉድለት፣ደላንታ ወረዳ ገቢዎች ጽ/ቤት ብር 11,187.36 ዋና ገንዘብ ያዥ ከ01/05/07-23/7/08 ዓ.ም ያንቀሳቀሱት የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ተመዛዝኖ የተገኘ የጥሬ ገንዘብ ጉድለት፣ ምስራቅ አማራ ውሃ ስራዎች ድርጅት ብር 274,235.82 የቀድሞው ግዥ ሰራተኛ ግዥ ለመፈፀም ያንቀሳቀሱት ሂሳብ ተመዛዝኖ የተገኘ የጥሬ ገንዘብ ጉድለት፣የመሀል ሳይንት ወረዳ ደንሳ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት ብር 73,370.88 የቀድሞው ዋና ገንዘብ ያዥ ከ13/08/03-17/06/06 ዓ.ም ያንቀሳቀሱት የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ተመዛዝኖ የተገኘ የጥሬ ገንዘብ ጉድለት፣አዲስ ፋና አጠ/1ኛ ደ/ት/ቤት ብር 19,428.07 ዋና ገንዘብ ያዥ ያንቀሳቀሱት የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ተመዛዝኖ የተገኘ የጥሬ ገንዘብ ጉድለት፣ግዳን ወ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 29,209.66 የቀድሞው የግዥ ሰራተኛ ግዥ ለመፈፀም በ2002 በጀት ዓመት ያንቀሳቀሱት ሂሳብ ተመዛዝኖ የተገኘ የጥሬ ገንዘብ ጉድለት፣ከ10 ሽህ ብር በላይ በመያዝ ከፍተኛውን ድርሻ ይሸፍናሉ፡፡ ከጥሬ ገንዘብ ጉድለት ጋር በተያያዘ ለግኝቶች በዋና ምክንያትነት የሚጠቀሱት፤
  - ለዕለት ሥራ እንቅስቃሴ ከሚያስፈልገው መጠን በላይ ጥሬ ገንዘብ በካዝና ማስቀመጥ፣
  - ገንዘብ ያዦች የራሳቸዉ መከታተያ የካዝና መቆጣጠሪያ መዝገብ እንዲይዙ አለማድረግ፣
  - በየጊዜው የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ በማድረግ ከተያዘው የመዝገብ ከወጪ ቀሪ ጋር እንዲመሳከር አለማድረግ፣
  - በዕለት ገቢ ሰብሳቢዎች የተሰበሰበው ገንዘብ ለባንክ ወይም ለዋና ገንዘብ ያዥ በወቅቱ ገቢ/ፈሰስ አለማድረግና ለረጅም ጊዜ በእጅ በማቆየት ለግል መጠቀሚያ መዋሉና

በመጨረሻም ጉደለት መገኘቱ፤

- በተለይ ለረዳት ገንዘብ ያዥና ለግዥ ሠራተኞች በቼክ የመክፈል ልምድን አለማዳበርና ከዋና ገ/ያዥ ጥሬ ገንዘብ በቅድሚያ ክፍያ ሰነድ በሚሰጥበት ወቅት ሂሳቡ ተወራርዷል አልተወራረደም በሚል የመካከድ ሁኔታ መፈጠር፤
- የገንዘብ ያዥ ለውጥ ሲደረግ በተገቢው ርክክብና የሂሳብ ምርመራ አለማስደረግ፤
- በወጪ ቫውቸሮችና ሌጀሮች የተሰራበት መጨረሻ ገጽ ላይ የመለያ ምልክትና ፊርማ (cut-off ) አለማድረግና አለመፈራረም፣
- የባንክ ሂሳብ ሌጀር አለመያዝና በየወሩ ባንክ ከሚልከው ሂሳብ መግለጫ ጋር አለማስታረቅ፣
- ከትምህርት ቤቶች እና ከታዳጊ ጤና ጣቢያዎችና ጤና ኬላዎች የሚሰበሰብ ገንዘብ ላይ ተገቢው ቁጥጥር አለማድረግና መድሃኒትና ገንዘብ በአንድ ባለሙያ መያዝ ብሎም የተሰበሰበ ገቢ ለረዥም ጊዜ በእጅ ላይ በማቆየት ለብክነት መዳረግ፤
- በባንክ ገቢ ደረሰኝ /ስሊፕ/ ላይ ቁጥር በመጨመር ባንክ ከገባው ገንዘብ አስበልጦ የገቢ ደረሰኝ ማስቆረጥ እና ልዩነቱን ለግል ጥቅም ማዋል፣
- በየደረጃው ያሉ የስራ ሃላፊዎች ስለ ጥሬ ገንዘብ አያያዝ የተዘረጋውን ስርዓት በማስፈፀም በኩል ውስንነት በመኖሩ፣
- ቀድሞ የተከፈሉና የተወራረዱ የሂሳብ ማስረጃዎችን /የፔይሮል/ ገጾችን ገንጥሎ እንደገና በወጪ በማጸደቅና በዚያው ልክ ገንዘብ ለግል በመውሰድ፤
- ጉድለትና ማጭበርበር በሚፈፅሙ አካላት ላይ የተጠያቂነት አሰራሩ አለመጠናከር፣
- በጥሬ ገንዘብ ሂሳብ የእለት እለት እንቅስቃሴ ላይ በፋይናንስ ኦፊሰሮችም ሆነ በውስጥ ኦዲተር የሚደረገው የውስጥ ቁጥጥር ማነስ የሚሉትን መጥቀስ ይቻላል፡፡

በመሆኑም ከገንዘብ ያዦች እና ንብረት ሰራተኛዎች የሚፈለገው ጉድለት ላይ ተገቢውን ክትትል በማድረግ ማስተካትና አጥፊዎች በህግ መጠየቅ እንዳለባቸው ባሳሰብነው መሰረት ብር 25,441.67 የተተካ ሲሆን ብር 218,953.72 በፍታብሔርና በወንጀል ክስ እንዲሁም ማስረጃ በማጣራት ሂደት ያለ መሆኑ የተገለፀልን ሲሆን ውሳኔው እየተጠበቀ ይገኛል፡፡

### 1.5.2 የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ኦዲት ማድረግ ያልተቻለባቸው መ/ቤቶች፣

የ2008 በጀት ዓመት ሂሣባቸው በመደበኛ ኦዲት ከተደረገት 221 መ/ቤቶች ውስጥ የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ኦዲት ለማድረግ ያልተቻለባቸው 64 (28.96%) መ/ቤቶች ዝርዝር ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

## የክልል ማዕከል መ/ቤቶች

1. ንግድ፣ኢንዱስትሪና ገበያ ልማት ቢሮ
2. ገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ቢሮ
3. አዲ አርቃይ ወረዳ ፍርድ ቤት
4. ፍትህ ቢሮ
5. አስተዳደርና ፀጥታ ጉዳዩች ቢሮ
6. ብቸና ቴክኒክና ሙያ ኮሌጅ
7. አዲስ ዘመን ቴክኒክና ሙያ ኮሌጅ
8. ቦሩ ሜዳ ሆስፒታል
9. ቦረና ማረሚያ ቤት
10. ተንታ ማረሚያ ቤት
11. ደብረ ብርሃን ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ
12. ወልድያ ሆስፒታል

### ምዕራብ ጎጃም ዞን አስተዳደር

13. ሜጫ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል
14. ወንበርማ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል
15. ሰከላ ወረዳ ገ/ኢ/ል/ጽ/ቤት
16. ቡሬ ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል
17. ፍኖተ ሰላም ከተማ አስ/ገ/አካ/ል/ጽ/ቤት

### ምስራቅ ጎጃም ዞን አስተዳደር

18. ጐንቻ ሲሶ እነብሴ ወረዳ ገ/ኢ/ል/ጽ/ቤት
19. ማቻከል ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል
20. ቢቡኝ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል
21. ደጀን ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል
22. ደጀን ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል
23. ሁለት እጁ እነሴ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል

### ሰሜን ጎንደር ዞን አስተዳደር

24. ሰሜን ጎንደር ዞን ገ/ኢ/ል/መምሪያ
25. ጣቁሳ ወረዳ ገ/ኢ/ል/ጽ/ቤት

### ደቡብ ጎንደር ዞን አስተዳደር

26. ሃሙሲት መሪ ማዘጋጃ ቤት
27. ጋሳይ መሪ ማዘጋጃ ቤት
28. መካነ እየሱስ ከተማ አስ/ገ/ኢ/ል/ጽ/ቤት
29. እብናት ከተማ ማዘጋጃ ቤት
30. ደራ ወረዳ ነ/ፋ/ደ/ስ ማዕከል
31. ደብረ ታቦር ከተማ አስ/ገቢዎች ጽ/ቤት

### አዊ ብሔረሰብ ዞን አስተዳደር

32. አንከሻ ጓጉሣ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል
33. ጓንጓ ወረዳ ገ/ኢ/ል/ትብብር ጽ/ቤት

### ደቡብ ወሎ ዞን አስተዳደር

34. ደሴ ከተማ አስ/ነ/ፋይ/ድ/ስ/ማ
35. ሳይንት ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ማዕከል
36. ቃሉ ወረዳ ነ/ፋይ/ድ/ስ/ማዕከል
37. ኩታበር ወረዳ ነ/ፋይ/ድ/ስ/ማዕከል
38. ተሁለደሬ ወረዳ ነ/ፋይ/ድ/ስ/ማዕከል
39. ከለላ ወረዳ ነ/ፋይ/ድ/ስ/ማዕከል
40. ቦረና ወረዳ ነ/ፋይ/ድ/ስ/ማዕከል
41. ወረባቦ ወረዳ ነ/ፋይ/ድ/ስ/ማዕከል
42. መሃል ሳይንት ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል
43. ሀይቅ ከተማ አስ /ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል
44. አልብኮ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል
45. ደላንታ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል

### ሰሜን ወሎ ዞን አስተዳደር

46. ቡግና ወ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማ
47. ወልድያ ከተማ አ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማ
48. ዋድላ ወ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማ
49. ላሊበላ ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማ
50. ግዳን ወ/ነ/ፋ/ድ/□/ማ

### ሰሜን ሸዋ ዞን አስተዳደር

51. አንጎለላና ጠራ ወ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማ
52. ደ/ብርሃን ከተማ አ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማ
53. አንኮበር ወ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማ
54. መንዝ ቀያ ገብሬል ወ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማ
55. እንሳሮ ወ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማ
56. ሸዋሮቢት ከተማ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማ

### ኦሮሞ ብሔረሰብ ዞን አስተዳደር

57. ጅሌ ጥሙጋ ወ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማ
58. ደዋ ጨፋ ወ/ነ/ፋ/ድ□ስ/ማ
59. አርጡማ ፉርሲ ወ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማ
60. ባቲ ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማ

### ዋግኸምራ ብሔረሰብ ዞን አስተዳደር

61. ሰሀላ ሰየምት ወ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማ
62. አበርገሌ ወ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማ
63. ዝቋላ ወ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማ
64. ጋዝጊብላ ወ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማ

ከላይ በተዘረዘሩት 64 መ/ቤቶች በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ሰኔ 30/2008 ዓ.ም ላይ ያለውን የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ከወጪ ቀሪ ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ ሲሆን ለዚህም ዝርዝር ምክንያቶች ቀጥለው ቀርበዋል፡-

- የተሟላ የሂሳብ መዝገብ /ሌጀር/ ተዘጋጅቶ የሂሳብ ምዝገባ ያልተደረገና ትክክለኛውን ከወጪ ቀሪ ሊያመለክት ባለመቻሉ፣
- በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በካዝና የሚገኝ ጥሬ ገንዘብና እንደጥሬ ገንዘብ የሚቆጠሩ ሂሳቦች የተሟላና ህጋዊ ቆጠራ ባለመደረጉ፡
- ገንዘቡ በአንድ ገንዘብ ያዥ ተይዞ እየተዳደረ ባለበት ሁኔታ የውስጥ ገቢን ሳይጨምር የመደበኛ ጥሬ ገንዘብ ሂሳብን ብቻ ነጥሎ ቆጠራ የሚደረግ በመሆኑ፤
- በገንዘብ ያዥ የሥራ መደብ ላይ በርካታ ሠራተኞች እየተለዋወጡ የጥሬ ገንዘብ ሂሣብን ያንቀሳቀሱ ሲሆን ርክክብ በተፈፀመበት ወቅት በገቢ ደረሰኞች፤ በወጪ ቫውቸሮችና በጥሬ ገንዘብ መከታተያ ሌጀሮች ላይ ርክክብ በተደረገበት ዕለት በጋራ በመፈራረም የመለያ /Cut-off/ ምልክት ያልተደረገ መሆኑእና ገንዘብ ያዦች በሚቀያየሩበት ወቅት ርክክብ ሲፈፀም የጥሬ ገንዘብ ሌጀር የሚያሳየው ከወጪ ቀሪ በቆጠራ እየተረጋገጠ ርክክብ የማይፈፀም መሆኑ፣
- ኦዲት አስደራጊዎች በኦዲት ወቅት የገቢና የወጪ ሂሣቡን መዝግበው እንዲያቀርቡ ተጠይቀው ምዝገባውን አጠናቀው ለማቅረብ አለመቻላቸው፣
- የተለያዩ የፕሮጀክት ሂሣቦች ከወጪ ቀሪያቸውን የሚያሣይ መቆጣጠሪያ የጥሬ ገንዘብ ሌጀር ያልተዘጋጀላቸው ሆኖ መገኘቱ፣
- ለረጅም ዓመታት እየተንከባለለ የመጣ የጥሬ ገንዘብ መቆጣጠሪያ ሌጀር እና የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ ልዩነት የፈጠረ ቢሆንም በኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች አማካኝነት መንስኤው ተለይቶ የማስተካከያ እርምጃ የማይወሰድ መሆኑ

ከላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ላይ ያለውን የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ከወጪ ቀሪ ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻሉባቸው ስለሆኑ መ/ቤቶቹ አሰራራቸውን እንዲያስተካክሉና በየጊዜውም በውስጥ ኦዲተሮቻቸው እየተከታተሉ የጥሬ ገንዘብ አስተደደራቸውን እንዲያሻሽሉ በየሪፖርቱ አሳስበናል፡፡

### 1.6. የገቢ ሂሳብ ኦዲት ውጤት

#### 1.6.1. የማጭበርበር ወንጀል የተፈፀመበት *የገቢ ሂሳብ እና ዘዴዎች፣*

በበጀት ዓመቱ ኦዲት ከተደረጉት መ/ቤቶች መካከል በ5 መ/ቤቶች ብር 3,178,432.91 የተለያዩ የማጭበርበር ዘዴዎችን በመጠቀም ለግል ጥቅም ውሎ ተገኝቷል፡፡ማጭበርበሩ የተፈጸመባቸው መ/ቤቶችና ዘዴዎቹ እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

- ስማዳ ወረዳ ገቢዎች ጽ/ቤት ብር 2,977,097.94 ከጥር 1/2003 ዓ.ም እስከ መስከረም 30/2009 ዓ.ም የተሰበሰበዉ ገቢ በትክክል ለወረዳዉ ፈሰስ ወይም ወደ ወረዳው ባንክ አካውንት ገቢ መደረግ ሲገባው ፈሰስ ሳይደረግ በገንዘብ ያዥ ተሰብስቦ ለግል ጥቅም የዋለ ገቢ፣
- ቦረና ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 115,913.53 በድርቅ ተጠቂ ለሆኑ ቀበሌዎች የመንገድ ቆረጣ ስራ

ማሽነሪ ክራይ ክፍያ ሲፈፀም ተቋራጩ በገቢዎች ጽ/ቤት የተጨማሪ እሴት ታክስ እንዲሰበስቡ ከተፈቀደው ደረሰኝ ውጭ በተጭበረበረ መንገድ ህጋዊ ያልሆነ ደረሰኝ አሳትመው በመሰብሰብ ለግል ጥቅም የዋለ ገቢ፣

- እንፍራንዝ ከተማ ንዑስ መዘጋጃ ቤት ብር 41,705.78 የገቢ ደረሰኝ በማበላለጥ፣በመሰረዝ፣አዲት የተደረገ ሰነድ በፍሉድ በማስተካከል የስመንብረት ዝውውር በማከናወን አላግባብ ለግል ጥቅም የዋለ ዋጋው ያልታወቀ መሬት እና ጥሬ ገንዘብ ብር 1,705.78 እና የቀበሌን ባህር ዛፍ በመሸጥ ለግል ጥቅም የዋለ ብር 40,000.00፣
- ተሁለደሬ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 40,250.66 ለገጠር ቀበሌዎች የመንገድ ተደራሽነት ስራ ለተሰራበት ማሽነሪ ክራይ ክፍያ ሲፈፀም ተቋራጩ በገቢዎች ጽ/ቤት የተጨማሪ እሴት ታክስ እንዲሰበስቡ ከተፈቀደው ደረሰኝ ውጭ በተጭበረበረ መንገድ ህጋዊ ያልሆነ ደረሰኝ አሳትመው በመሰብሰብ ለግል ጥቅም የዋለ ገቢ፣
- ቦረና ወረዳ ጨሬ ት/ቤት ብር 3,465.00 የገቢ ደረሰኝ ሳይቆረጥ ተሰብስቦ በገንዘብ ያዥ ለግል ጥቅም የዋለ የትምህርት ቤት ሂሳብ፣

በመሆኑም ድርጊቱን ከፈጸሙት አካላት የሚፈለገው የህዝብ ሀብት ተገቢውን ክትትል በማድረግ ማስተካትና አጥፊዎች በህግ መጠየቅ እንዳለባቸው ባሳሰብነው መሰረት ብር 2,977,097.74 በፍታብሔርና በወንጀል ክስ ሂደት ላይ ያለ መሆኑ የተገለፀልን ሲሆን ውሳኔው እየተጠበቀ ይገኛል፡፡

### 1.6.2 ያለተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ተሰብስቦ ለግል ጥቅም የዋለ የተጨማሪ እሴት ታክስ፣

የተጨማሪ እሴት ታክስን አስመልክቶ በወጡ ደንብና መመሪያዎች መሠረት ማንኛውም በተጨማሪ እሴት ታክስ ከፋይነት ደረጃ የሚገኝ ድርጅት በከፋይነት ተመዝግቦ እቃ/አገልግሎት ሲያቀርብ ለክፍያው የቫት ደረሰኝ/ማስረጃ የማቅረብ ግዴታ ያለበትና ግዥ የሚፈጽሙ አካላትም ማስረጃው እንዲቀርብላቸው የማድረግ ሃላፊነት የተጣለባቸው ቢሆንም በ9 መ/ቤቶች ብር 2,916,894.29 የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ሳይቀርብ ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡ የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ሳይቀርብ ክፍያ የተፈፀመባቸው መ/ቤቶች ዝርዝር፡-

- **ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ብር 1,759,457.54** የስታዲዮም ግንባታ ከክፍያ ቁጥር-2 እስከ ክፍያ ቁጥር-41 ድረስ ለተቋራጩ ክፍያ ሲፈፀም ተቀንሶ ያልቀረ የተጨማሪ እሴት ታክስ፣
- **ስትዳደርና ፀጥታ ጉዳዮች ቢሮ ብር 407,614.41** ከብረታ ብረትና ኢንጅነሪን ኮርፖሬሽን ጥይት ግዥ ሲፈፀም ከክፍያ ያልተሰበሰበ የተጨማሪ እሴት ታክስ፣
- **ወንበርማ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 297,768.50** በቁጥር መፍ/መ/ቁ/0116423 በቀን 30/10/08 ዓ.ም በወረዳው ፍርድ ቤት በተሰጠ ትዕዛዝ መሰረት ለተስፋ ንጉስና ጓደኞቹ የህንፃ ስራ ተቋራጭ ማህበራት እና በቁጥር በፍ/መ/ቁ/0304244 በቀን 19/05/08 ዓ.ም የባህር ዳርና አካባቢዋ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ባዘዘው መሰረት ለአብክመ ቤቶች ልማትና ግንባታ አክሲዎን ማህበር ክፍያ ሲፈፀም የተጨማሪ እሴት ታክስ ሳይሰበሰብ የተከፈለ፣

- **አርጡማ ፉርሲ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 180,593.33** በወረዳው በአዳ ባላ አጠ/2ኛ ደ/ት/ቤት ግንባታ ሲፈፀም እና ለፍትህ ጽ/ቤት የቢሮ ግንባታ ሲፈፀም የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ሳይቀርብ የተፈፀመ፣
- **ቢብኝ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 142,159.19** ለዋብር 2ኛ/ደ/ት/ቤት የአስተዳደር ቢሮ እና ቤተ-መጽሀፍት ለተሰራበት ክፍያ ከተቋራጩ ሲፈፀም የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ያልቀረበ፤
- **ዳዋ ጨፋ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 48,882.49** ከወረዳው ጤና ጥበቃ ጽ/ቤት በሊትር ቀበሌ ላፍቶ ጤና ኬላ የመፀዳጃ ቤት ግንባታ ሲፈፀም፣ለሩፊሲ 2ኛ/ደ/ት/ቤት ለአስተዳደር ቢሮ ግንባታ ክፍያ ሲፈጸም የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ሳይቀርብ የተፈፀመ፣
- **መተማ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 48,199.03** የወረዳው ሴክተር መ/ቤቶች ቢሮ ግንባታ ለተከናወነበት ክፍያ ሲፈፀም ከተቋራጩ የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ያልቀረበ፤
- **አንጎለላና ጠራ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 16,972.00** በገጠር መንገድ ጽ/ቤት የድልድይ ግንባታ ሲፈጸም የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ሳይቀርብ የተፈፀመ፣
- **ነፋስ መውጫ ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 15,247.80** ለከተማ አስተዳደሩ ሴክተር መ/ቤቶች የተለያዩ የጽህፈት መሣሪያዎች ግዥ ክፍያ ሲፈፀም ከአቅራቢው የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ሳይቀርብ የተገኘ፣

በመሆኑም ታክሱ ከመንግስት ተቋማት ያለተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ የተሰበሰበና ለግል ጥቅም የዋለ በመሆኑ ተቋራጮች ታክሱን ለገቢ ሰብሳቢው አካል ገቢ አድርገው ማስረጃ እንዲያቀርቡ መደረግ እንዳለበት ታክሱን ለመመለስ ፈቃደኛ ካልሆኑ በሚመለከተው የፍትህ አካል ክስ በመመስረት ከተጠቃሚው የተሰበሰበው የተጨማሪ ለሴት ታክስ ወደ መንግስት ካዝና ገቢ የሚሆንበት ሁኔታ እንዲመቻች በሪፖርታችን ብናሳስብም የተወሰደውን እርምጃ የሚያሳይ ምላሽ አልደረሰንም፡፡

**1.6.3. ያልተሰበሰበ (በውዝፍ) የሚገኝ ቁጢ፤**

**የ2008 በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት ከተደረገ 268 መ/ቤቶች □ስዓ በ107 መ/ቤቶች ብር 30,395,650.08** ሥራ ላይ ባለው የገቢ አሰባሰብ ሥርዓት መሠረት ቁጢ□ በ□ቅቱ ሳ□ሰበሰብ ተገኝቷል፡፡ □ር□ሩም እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

**ሠንጠረዥ 6 በውዝፍ የሚገኝ ቁጢ፣**

| ተ.ቁ | ኦዲት ተደራጊው መ/ቤት | የ2007 በ□□አ □ተኛ/ያልተሰበሰበ ገቢና ቅጣት ሂሣብ | | | የ2008 በውዝፍ የሚገኝ/ያልተሰበሰበ ገቢና ቅጣት ሂሣብ | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | የመ/ቤት ብዛት | የገንዘቡ ልክ | % | የመ/ቤት ብዛት | የገንዘቡ ልክ | % |
| 1 | □□ልል መ/ቤቶች | 5 | 209,079.70 | | 8 | 871,387.36 | 2.87 |
| 2 | ባህር ዳር ከተማ | | - | | | | |
| 3 | ምክ/□ጸም | 6 | 105,786.04 | | 7 | 1,046,715.93 | 3.44 |
| 4 | ምሥ/□ጸም | 6 | 89,750.03 | | 14 | 8,089,715.65 | 26.61 |
| 5 | ሰሜን ጎንደር | 6 | 50,487,477.56 | | 4 | 2,442,436.04 | 8.04 |
| 6 | ደ/ጎንደር | 4 | 27,657.07 | | 9 | 4,441,302.75 | 14.61 |

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 7 | ሰሜን ወሎ | 6 | 391,469.08 | | 9 | 1,865,672.89 | 6.14 |
| 8 | □ቡብ □ሎ | 6 | 79,867.61 | | 16 | 1,767,902.75 | 5.82 |
| 9 | ሰሜን ሸዋ | 15 | 1,156,930.08 | | 22 | 5,223,594.88 | 17.18 |
| 1ወ | አዊ ብሔረሰብ | 4 | 3,026,647.54 | | 6 | 2,166,893.97 | 7.13 |
| 11 | ዋግ ኽምራ | 5 | 405,083.09 | | 8 | 710,784.11 | 2.34 |
| 12 | ኦሮሞ ብሔረሰብ | 5 | 3,348,511.80 | | 4 | 1,769,243.75 | 5.82 |
| **ትምር** | | **68** | 59,328,259.60 | | **107** | **30,395,650.08** | **100** |

*ከሠንጠረዡ መረዳት እንደሚቻለ□ የ2008 በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት ከተደረጉ 268 መ/ቤቶች □ስዓ በ107 መ/ቤቶች ብር* 30,395,650.08 *ባለው የገቢ አሰባሰብ ሥርዓት መሠረት ገቢ በ□ቅቱ ሳ□ሰበሰብ በውዝፍነት ተገኝቷል፡፡ ከፍተኛ ያልተሰበሰበ የመንግሥት ገንዘብ ከሚታይባቸው ዞኖች መካከል ምስራቅ ጎጃም ዞን አስተዳደር ብር* 8,089,715.65(26.6%) *፣ሰሜን ሸዋ ዞን አስተዳደር ብር* 5,223,594.*88(17.18*%) *እና ደቡብ ጎንደር ዞን አስተዳደር ብር* 4,441,302.75(14.61%) *ከፍተኛውን ትርሻ ይይዛሉ፡፡*

*መንግሥት የበጀት ዓመቱን ሥራ ለማከናወን ዕቅድ የሚነድፈው ገቢ የመሰብሰብ ሥልጣን ከተሰጣቸው መ/ቤቶች ይሰበሰባል ተብሎ የታቀደውን በታሳቢነት በመያዝ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ስለሆነም በገቢ አሰባሰብ ላ□ መንግሥት ያደረጋቸውን የገቢ ግብር ማሻሻያዎች ግምት ውስጥ በማስገባት ገቢን በወቅቱ መሰብሰብ ተገቢው ትኩረት ሊሰጥ እንደሚገባ ለየመ/ቤቶች በተላከው ሪፖርት ተገልጿል፡፡ ያልተሰበሰበ ገቢ ተብሎ ከተያዘው ዉስጥ ብር* 27,308.00(0.09%) *ብቻ ስለመሰብሰቡ በተሰጠው የኦዲት ሪፖርት ግብረ መልስ የተገለጸ ሲሆን ቀሪው ብር* 30,368,342.08 *የተሰበሰበ ስለመሆኑ መልስ ያልተሰጠበትና መልስ ቢሰጥበትም እስከዚህ ሪፖርት ጥንቅር ሰኔ* 23/2009 *ዓ/ም ድረስ ስለመሰብሰቡ አልተገለፀም፡፡ (ዝርዝሩን አባሪ* 2 *ይመልከቱ፡፡)*

### 1.6.4.ያለማስረጃ የተሰበሰበ ገቢ፤

*ማንኛውም ገቢ ከመሰብሰቡ አስቀድሞ ስለገቢው ህጋዊነት እና ስለመጠኑ ትክክለኛነት (ታሪፍ) የሚያስረዳ እንደ መድሃኒት ማዘዣ፤የገቢ አሰባሰብ ውሳኔ ወዘተ ምን ያህል ሊሰበሰብ እንደሚገባ የሚገልጽ ማስረጃ ሊኖር ሲገባ ይህ በሌለበት ሁኔታ ከ*1 *መ/ቤት በድምሩ ብር* **39,588.87** *የገቢ ሂሳብ ተሰስብቦ ተገኝቷል፡፡ ያለማስረጃ ገቢ የተሰበሰበት መ/ቤት ፍኖተ-ሰላም ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ሲሆን ምንጩ ያልታወቀና በሚጠበቀው መጠን ስለመሰብሰቡ ለማረጋገጥ ያልተቻለ ገቢ ሰብስቦ ተገኝቷል፡፡*

*በመሆኑም ለገቢው አግባብነት ያለውና መሰብሰብ ያለበትን መጠን የሚያሳይ ማስረጃ እንዲያያዝለት ለመ/ቤቱ በኦዲት ሪፖርት አሳስበናል፡፡ሆኖም ስለገቢው መጠን ትክክለኛነትና ማስረጃው ስለመያዙ በምላሽ አልተገለጸም፡፡*

### 1.6.5. ያልተሰበሰበ 2% የንግድ ስራ ትርፍ ግብር፤

*በገቢ ግብር አዋጅና ደንብ እንደተመለከተው ከተወሰነ መጠን በላይ የሆነ የእቃና አገልግሎት ክፍያ ሲፈጸም ከተከፋይ ሂሣብ ላይ ተቀንሶ መሰሠብሰብ የሚገባው* 2% *የንግድ ስራ ትርፍ ግብር ከ*19 *መ/ቤቶች በድምሩ ብር* **1,362,800.12** *ሳይሰበሰብ ተገኝቷል፡፡ ገቢው ከየሚመለከታቸው ላይ ክትትል*

ተደርጎ እንዲሰበሰብ በየሪፖርቶቹ ብናሳስብም መሰብሰቡን የሚገልጽ ማስረጃ በግብረ መልስ ያልተገለፀ ስለሆነ ያልተሰበሰበ የንግድ ስራ ትርፍ ግብር በምን ሁኔታ ላይ እንዳለ ለማወቅ አልተቻለም፡፡

### 1.6.6 ለኦዲት ሊቀርቡ ያልቻሉ ገቢ የተሰበሰበባቸው ደረሰኞች፣

ገቢ በትክክል መሰብሰቡን ለማረጋገጥ ገቢ የተሰበሰበባቸው ደረሰኞች ለኦዲት ተሟልተው እንዲቀርቡ ተጠይቀው በ62(28.05%) መ/ቤቶች ብር 18,155,823.39 የያዙ የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኞች ለኦዲት ሊቀርቡ ባለመቻላቸው የገቢውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

የገቢ ደረሰኞችን ለኦዲት ካላቀረቡት መ/ቤቶች መካከል ደብረ ማርቆስ ከተማ አስተዳደር ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 3,627,347.75 የያዙ ብዛት 44 ጥራዝ የመደበኛ ገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኞች፣አንከሻ ጓጉሳ ወረዳ /ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 2,386,251.03 የያዙ የስፖርት ምክር ቤት፣የእርሻ ስራ ገቢ ግብር እና የመደበኛ ገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኞች፣ ፎገራ ወረዳ /ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 1,170,345.00 የያዙ የስፖር ምክር ቤት እና የእርሻ ስራ ገቢ ግብር መሰብሰቢያ ደረሰኞች፣ተሁለደሬ ወረዳ /ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 997,447.00 የያዙ ብዛት 28.45 ጥራዝ የስፖርት ምክር ቤት እና የመደበኛ ገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኞች ፣መተማ ወረዳ /ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 980,395.74 የያዙ የመደበኛ ገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኞች፣ምዕራብ እስቴ ወረዳ /ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 666,690.53 የያዙ የመደበኛ፣የስፖርት ምክር ቤት እና የእንስሳት ፈንድ የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኞች፣እናርጅ እናውጋ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 659,810.00 የያዙ የስፖርት ምክር ቤት እና የእርሻ ስራ ገቢ ግብር የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኞች፣ወንበርማ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 619,615.00 የያዙ የስፖርት ምክር ቤት እና የእርሻ ስራ ገቢ ግብር የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኞች ፣ሲያ ደብርና ዋዩ /ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 574,030.00 የያዙ ብዛት ባለማቅረብ ለኦዲት 208.2 ጥራዝ የስፖርት ምክር ቤት እና የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኞች ከብር 500,000.00 በላይ የያዘ ደረሰኝ ለኦዲት ባለማቅረብ ከፍተኛውን ድርሻ ይይዛሉ፡፡

ይህም ለኦዲት ባልቀረቡት ደረሰኞች ገቢው በትክክል ለመሰብሰቡ ባለመረጋገጡ በጉዳዩ ላይ አስተያየት ለመስጠት ገደብ የተጣለበትና ማጭበርበር ተሰርቶባቸው ይሁን አይሁን ጥርጣሬን ያሳደረ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ለኦዲት ሊቀርቡ ካልቻሉ ገቢ የተሰበሰበባቸው ደረሰኞች ዉስጥ ብር 405,341.53(2.23%) የያዙ ገቢ ደረሰኞች ብቻ ቀርበው በውስጥ ኦዲት የተረጋገጡ ስለመሆናቸው በተሰጠው የኦዲት ሪፖርት ግብረ መልስ የተገለጸ ሲሆን ቀሪው ብር 17,750,481.86 ገቢ የተሰበሰበባቸው ደረሰኞች የገቢው ትክክለኛነት በውስጥ ኦዲተሮች እንዲረጋገጥና ደረሰኞቹን በሰወሩ/ባላቀረቡ ሠራተኞችና ኃላፊዎች ላይ ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ በየሪፖርቶቹ ብናሳስብም የተወሰደው እርምጃ እስከዚህ ሪፖርት ጥንቅር ሰኔ 23/2009 ዓ/ም ድረስ ምላሹ አልተገለፀም፡፡

## 1.7. የተሰብሳቢ ሂሣብ ኦዲት ውጤት፤

### 1.7.1. በወቅቱ ያልተሰበሰበ (ያልተወገደ) ተሰብሳቢ ሂሣብ፤

የ2008 በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት ከተደረጉ መ/ቤቶች ውስጥ በ117 መ/ቤቶች ብር 1,616,834,934.47 በወቅቱ በፋይናንስ የአሠራር ስርዓት መሠረት ሣይሰበሰብ (ሳይወገድ) ተገኝቷል፡፡ (ዝርዝሩም እንደሚከተለው ቀርቧል)፤

ሠንጠረዥ 7 በወቅቱ ያልተሰበሰበ /ያልተወገደ/ ሂሣብ፤

| ተ.ቁ | ኦዲት ተደራጊው መ/ቤት | 2007 ሂሣብ | | | 2008 ሂሣብ | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | የመ/ቤት ብዛት | የገንዘቡ ልክ | % | የመ/ቤት ብዛት | የገንዘቡ ልክ | % |
| 1 | የክልል መ/ቤቶች | 18 | 234,485,060.48 | 28.31 | 25 | 434,628,972.91 | 26.88 |
| 2 | ባሕር ዳር ከተማ | | - | 0 | | | |
| 3 | ምክ/□ጸም | 4 | 3,382,928.46 | 0.41 | 12 | 157,517,032.34 | 9.74 |
| 4 | ምሥ/□ጸም | 12 | 91,103,258.64 | 11 | 13 | 90,425,312.28 | 5.59 |
| 5 | ሰሜን ጎንደር | 7 | 83,978,494.27 | 10.13 | 5 | 192,279,192.51 | 11.89 |
| 6 | ደ/ጎንደር | 8 | 97,363,153.95 | 12 | 6 | 88,942,937.65 | 5.50 |
| 7 | አዊ ብሔረሰብ | 6 | 39,735,281.26 | 4.8 | 7 | 132,521,507.74 | 8.20 |
| 8 | ሰሜን ወሎ | 9 | 69,313,090.62 | 8.37 | 10 | 107,544,159.79 | 6.65 |
| 9 | □ቡብ □ሎ | 11 | 96,543,582.24 | 11.91 | 12 | 240,954,603.02 | 14.90 |
| 10 | ሰሜን ሸዋ | 11 | 60,296,687.38 | 6.07 | 15 | 82,281,244.77 | 5.09 |
| 11 | ኦሮሞ ብሄረሰብ | 3 | 22,601,971.37 | 3 | 5 | 45,831,955.68 | 2.84 |
| 12 | ዋግኽምራ ብሔረሰብ | 5 | 29,477,773.75 | 4 | 7 | 43,908,015.78 | 2.72 |
| | ድምር | **94** | **828,281,282.42** | **100** | **117** | **1,616,834,934.47** | **100** |

በአጠቃላይ በወቅቱ ያልተሰበሰበ /ያልተወገደ/ ተሰብሳቢ ሂሳብ ካለፈው ዓመት ብር 828,281,282.42 ጋር ሲነፃፀር በ2008 በጀት ዓመት ሂሣብ ላይ የተገኘው በመ/ቤቶች ቁጥር 23 እና በገንዘብ መጠን በብር 788,553,652.05 ጨምሮ ተገኝቷል፡፡ ይህም በወቅቱ ያልተሰበሰበ /ያልተወገደ/ ተሰብሳቢ ሂሳብ ክምችት እየጨመረ መሄዱን ያመለክታል፡፡

ከላይ በሠንጠረዥ እንደተመለከተው በወቅቱ ያልተሰበሰበ /ያልተወገደ/ ከፍተኛ ተሰብሣቢ ሂሣብ ከሚታይባቸው መ/ቤቶች መካከል አብክመ ቴክኒክና ሙያ ኢንተርፕራይዝ ልማት ቢሮ /MDG/ ብር 173,652,661.02፣ ደባርቅ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 134,528,952.12፣ ኮምቦልቻ ከተማ አስ/ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 99,276,454.57፣ አብክመ ፖሊስ ኮሚሽን ብር 98,217,706.93፤ እብናት ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 51,899,335.14፣ ደቡብ ወሎ ዞን አስተዳደር ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 48,761,908.23፣ ግብርና ቢሮ /MDG/ ብር 44,672,654.09፣ አንከሻ ጓጉሳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 38,232,293.81፣ ጤና ጥበቃ ቢሮ /MDG/ ብር 35,841,202.74፣ ዳንግላ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 35,408,629.34፣ ምዕራብ ጎጃም ዞን ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 34,460,452.82፣ ጎንደር ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 32,409,155.14፣ ደቡብ ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ብር 30,866,356.75፣ ጃማ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 28,693,122.27፣ፋግታ ለኮማ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 28,620,419.03፣ ወልድያ ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 27,076,088.18፣ኦሮሞ ብሄረሰብ ዞን ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 26,894,697.04፣ቡሬ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 26,245,804.44 እና ጎንቻ ሲሶ እነብሴ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 23,676,689.01 ከብር 20 ሚሊዩን በላይ የተሰብሳቢ ክምችት በመያዝ ከፍተኛውን ድርሻ ይሸፍናሉ፡፡

ተሰብሳቢ ሂሳቦች የራሳቸው የተወሰነ የመሰብሰቢያ ወይም የመወገጃ ጊዜ እንዳላቸውና በመመሪያው መሠረት ተገቢው እርምጃ መወሰድ እንዳለበት ከገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ቢሮ በቁጥር 6/2004 በክፍል 4

በተላለፈው መመሪያ የተገለጸ ቢሆንም አንዳንድ መ/ቤቶች ተግባራዊ ባለማድረጋቸው ጊዜው በዘገየ ቁጥር ያለመሰብሰብ ዕድሉ እየሠፋ ስለሚሄድ መመሪያው በሚያዘው መሰረት ተግባራዊ ሊደረግ እንደሚገባ በሪፖርቶቻችን ገልጸናል፡፡

ሆኖም ስለተወሰደው እርምጃ በተሰጠው ምላሽ ብር 88,550,706.86(5.48%) **ከኦዲት በኋላ የተሰበሰበ መሆኑ የተገለፀ ሲሆን ቀሪው ብር** 1,528,284,227.61 ስለተወሰደው እርምጃ ባለመገለጹ ይህ ዘገባ እስከተጠናቀረበት ጊዜ ድረስ ተሰብሳቢ ሂሳቡ ስላለበት ደረጃ የታወቀ ሁኔታ የለም፡፡

በሌላ በኩል የተሰብሳቢ ሂሳብ ትክክለኛነት እንዳስፈላጊነቱ በሚመለከተው 3ኛ ወገን ማረጋገጫ እንዲቀርብለት የሚደረግ ሲሆን በበጀት ዓመቱ ስለትክክለኛነቱ ከ3ኛ ወገን (ከሚሰበሰብባቸው አካላት) ለማረጋገጥ ከተጠየቁት የተሰብሳቢ ሂሳቦች መካከል በ16 መ/ቤቶች ብር 70,481,952.57 የ3ኛ ወገን ማረጋገጫ አልቀረበለትም፡፡ከዚህ ተሰብሳቢ ሂሣቦች መካከል ቃሉ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 25,516,304.90፣ ከለላ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 19,690,767.85፣ ወግዲ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 8,445,903.46፣ ደቡብ ጎንደር ዞን አስ/ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 8,229,207.13 እና ወንበርማ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 2,353,628.05 ፣ ከብር 2 ሚሊዮን በላይ የሦስተኛ ወገን ማረጋገጫ ያልተገኘላቸውን ተሰብሳቦውች በመያዝ ከፍተኛውን ድርሻ ይዘዋል፡

ይህም ሂሳቡ ትክክለኛ ተሰብሳቢና ባለቤት ያለው ስለመሆኑ በማረጋገጥ መ/ቤቶቹ ተሰብሳቢው ሂሳብ የተያዘበትን አግባብ በመገምገም በሚገኘው ውጤት መሠረት ተገቢውን እርምጃ እንዲወስዱ በሪፖርት ያስገነዘብን ቢሆንም የተወሰደውን እርምጃ አስመልክቶ የተሰጠ ምላሽ የለም፡፡

**1.7.2 ማስረጃ ያልቀረበለት ተሰብሳቢ ሂሣብ፤**

የ2008 በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት ከተደረጉ መ/ቤቶች ውስጥ 3 መ/ቤቶች ብር 708,125.86 ትክክለኛ ተሰብሳቢ ሂሳብ ስለመሆኑ የሚያስረዳ ሠነድ (መቸ እንደተሰጠ፣ ከማን እንደሚሰበሰብ እና ለምን እንደተሰጠ ምንጩ ሳይታወቅ) ሳይኖረው በተሰብሳቢ ሂሳብ ተይዞ ተገኝቷል፡፡ ይኸው ሂሳብ የተገኘባቸው መ/ቤቶች ይልማና ዴንሳ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 602,142.68፣ ምስራቅ ጎጃም ዞን ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 37,980.21 እና ሰቆጣ ዙሪያ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 68,002.97 ናቸው፡፡ ከተጠቀሰዉ ሂሳብ ዉስጥ የነጠላ ፋይናንስ አደረጃጀት በተጀመረበት ወቅት ከየሴክተሮቹ ሂሣብ ክፍል በርክክብ የመጣ፣የግብዓትና የተዘዋዋሪ ብድር ሂሣብ መሆኑንና በወቅቱ ሂሳቡ ከማን እንደሚሰበሰብ መቼ እና ለምን የተሰጠ እንደሆነ የሚያሳይ ሰነድ/ማስረጃ እንዳልተያያዘለት ተመልክቷል፡፡

በመሆኑም ለሂሳቡ ትክክለኛ ዝርዝር ደጋፊ ማስረጃ ካለ እንዲያያዝና በየባለዕዳዎቹ ስም ተለይቶ ተይዞና ክትትል ተደርጐ እንዲሰበሰብ ወይም በመመሪያው መሰረት ከመዝገብ እንዲወገድ የኦዲት አስተያየት ተሰጥቷል፡፡ ሆኖም ይህ ሪፖርት እስከተጠናቀረበት ጊዜ ድረስ የተወሰደውን እርምጃ የሚገልጽ ምላሽ አልደረሰም፡፡

### 1.7.3 በተቀጽላ ሌጀር ያልተመዘገበ ተሰብሳቢ ሂሳብ፤

የ2008 በጀት ዓመት ሂሳባቸው ኦዲት ከተደረጉት መ/ቤቶች መካከል በ51 መ/ቤቶች ብር 295,927,726.30 የመንግስት የሂሣብ አያያዝ ሥርዓትን በመተላለፍ የተሰብሳቢ ሂሣብ ተቀጽላ ሌጀር ሣይዘጋጅለት ተገኝቷል፡፡ ከዚህ ተሰብሳቢ ሂሳብ ውስጥ በግብረ መልስ እንደተረጋገጠው ብር 70,559.93 ተቀጽላ ሌጀር የተዘጋጀለት መሆኑ የተገለፀ ሲሆን ቀሪው ብር 295,857,166.37 ይህ ሪፖርት እስከተጠናቀቀበት ሰኔ 23/2009 ዓ.ም ድረስ የተሰጠ ግብረ መልስ ባለመቅረቡ በምን ሁኔታ ላይ እንደሚገኝ አልታወቀም፡፡

**ሠንጠረዥ 8 በተቀጽላ ሌጀር ያልተመዘገበ ተሰብሳቢ ሂሳብ፤**

| ተ.ቁ. | በክልል ማዕከላትና ዞን | የመ/ቤቱ ብዛት | የገንዘቡ ልክ | % |
|---|---|---|---|---|
| 1 | የክልል መ/ቤቶች | 7 | 29,257,281.84 | 9.89 |
| 2 | ባህር ዳር ከተማ | - | - | 0 |
| 3 | ምዕራብ ጎጃም | 6 | 44,693,545.14 | 15.10 |
| 4 | ምስራቅ ጎጃም | 7 | 10,555,611.56 | 3.57 |
| 5 | ሰሜን ጎንደር | 2 | 22,315,835.84 | 7.54 |
| 6 | ሰሜን ወሎ | 4 | 12,362,664.01 | 4.18 |
| 7 | ሰሜን ሸዋ | 2 | 1,524,593.90 | 0.51 |
| 8 | ደቡብ ጐንደር | 4 | 45,026,693.17 | 15.22 |
| 9 | ደቡብ ወሎ | 10 | 86,480,890.84 | 29.22 |
| 10 | ኦሮምያ ብሔረሰብ ዞን | 2 | 13,047,443.26 | 4.41 |
| 11 | አዊ ብሔረሰብ ዞን | 5 | 26,800,707.00 | 9.05 |
| 12 | ዋግኽምራ | 2 | 3,862,459.74 | 1.31 |
| | **ደምር** | **51** | **295,927,726.30** | **100** |

ከሠንጠረዡ መመልከት እንደሚቻለው የተሰብሳቢ ሂሣብ ተቀጽላ ሌጀር አለመዘጋጀትን በተመለከተ አብክመ ማረሚያ ቤቶች ኮሚሽን ብር 27,088,219.50፣ ፎገራ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 23,505,886.81፣ ሊቦ ከምከም ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 20,672,270.67፣ወንበርማ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 18,743,740.30፣ ቦረና ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 18,408,822.76፣ ጣቁሳ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 17,438,131.36፣ ደሴ ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 15,807,046.20፣ ጓንጓ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 15,439,533.46፣ ይልማና ዴንሳ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 13,860,624.24፣ ጅሌ ጥሙጋ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 1,241,966.39፣ መሀል ሳይንት ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 11,705,059.70፣ ወግዲ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 10,574,489.98፣ ከብር 10 ሚሊዮን በላይ በመያዝ ከፍተኛውን ድርሻ ይዘው ይገኛሉ፡፡

ተቀጽላ ሌጀር ያልተዘጋጀለትን ተሰብሳቢ ሂሣብ በተመለከተ ገንዘቡ ከማን እንደሚፈለግ ገላጭ ባለመሆኑና በጥቅሉ ስለተመዘገበ ባለቤቱን አውቆ ከሚመለከተው ላይ ለመሰብሰብ ወይም ለማስወገድ የማያስችል በመሆኑ የተሻሻለውን የሂሣብ አያያዝ ሥርዓት በመከተል በየስሙ ተለይቶ የተቀፅላ ሌጀር ሊዘጋጅለትና ክትትል እየተደረገ ሊሰበሰብ/ሊወገድ/ እንደሚገባው በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡ (አባሪ 2 ይመልከቱ)፤

## 1.8. □ወጪ ሒሣብ ኦዲት ውጤት፣

*የ2008 በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት ከተደረጉ መ/ቤቶች የተገኙ ዋና ዋና የወጪ ሂሳብ የአሠራር ግኝቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡*

### *1.8.1 የማጭበርበር ወንጀል የተፈፀመበት የወጪ ሂሳብ እና ዘዴዎች፣*

በበጀት ዓመቱ ኦዲት ከተደረጉት መካከል በ15 መ/ቤቶች ብር 845,755.30 የተለያዩ የማጭበርበር ዘዴዎችን በመጠቀም ለግል ጥቅም ውሎ ተገኝቷል፡፡ ማጭበርበሩ የተፈጸመባቸው መ/ቤቶችና የአፈፃፀም ዘዴዎቹ እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

- ***ሜጫ ወረዳ ጤና ጥበቃ እና ግብርና ጽ/ቤት ብር 311,572.00፣*** ከጤና ጥበቃ በጀት ምንም ዓይነት ስልጠና በዱር ቤቴ ከተማ ስልጠና ሳይሰጥ ተካሂዷል በሚል አለአግባብ የተከፈለ የስልጠና አበል ብር 37,800.00 ፣ከጤና ጥበቃ በጀት በባህር ዳር ከተማ አዝዋ ሆቴል ስልጠና ተሰጥቷል በሚል ያለአግባብ የተከፈለ የስልጠና አበል ብር 52,800.00 ፣ በፍራፍሬ ልማት ለተደራጁ ወጣቶች ስልጠና ሳይሰጥ ስልጠና ተሰጥቷል በሚል የተከፈለ ብር 31,250.00፣በለቀቁ ሰራተኞች ስም ወጪ ተደርጎ ለግል ጥቅም የዋለ የውሎ አበል ብር 6,150.00፣አለአግባብ ለወረዳው ስትሪንግ ኮሚቴ የተከፈለ የውሎ አበል ብር 22,050.00፣ ዳንግላ ቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ኮሌጅ ስልጠና ሳይሰጥ እንደተሰጠ ተደርጎ ማስረጃ በማቅረብ ያለአግባብ የተከፈለ ብር 148,890.00 እና ብር 12,632.00 ስልጠናው ወተት አባይ ተከናውኖ በባህር ዳር ከተማ ታሪፍ የተከፈለ የስልጠና አበል፣
- ***ጓንጓ ወረዳ ገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ጽ/ቤት ብር 186,976.10*** በውሉ መሠረት ችግኝ ሳይጭኑ እንደጫኑ ተደርጎ ተከፍሎ ለግል ጥቅም የዋለ ሂሳብ፣
- ***ጎንጅ ቆለላ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 101,341.89*** ሰራተኞች ቢሮ ውስጥ በስራ ገበታቸው እያሉ መስክ ሳይወጣ እና በተመሳሳይ ቀናት በድጋሜ፣እንዲሁም ስልጠና ሳይሰጥ ስልጠና ተሰጥቷል በሚል ተከፍሎ ለግል ጥቅም የዋለ የመንግስ ገንዘብ፣
- ***አዲአርቃይ ወረዳ ፍርድ ቤት ብር 63,021.44*** ሰራተኞች ቢሮ ውስጥ በስራ ገበታቸው እያሉ መስክ ሳይወጣ፣ ስልጠና ከተሰጠበት ከተማ የውሎ አበል ታሪፍ በላይ የተፈፀመ፣ለማይመለከተው ባለሙያ የተከፈለ ውሎ አበል፣ ከመመሪያ ውጭ የተፈፀመ የትርፍ ስዓት ክፍያ፣ ለሚመለከታቸው ሰራተኞች የደንብ ልብስ መስጠት ሲገባው አላግባብ ውሎ አበል እንዲሰጥ የተደረገ፣
- ***ወገራ ወረዳ ጤና ጥበቃ ጽ/ቤት ብር 54,054.75*** ለስልጠና  እና ለመስክ ስራ ሳይወጣ አላግባብ ተከፍሎ የተገኘ፣ ቅዳሜና እሁድ እንዲሁም በትርፍ ሰዓት ለተሰራ ስራ የውሎ አበል ወይም የስልጠና አበል እንዲከፈል የሚደነግግ መመሪያ በሌለበት የተከፈለ እና ተግባሩ ከሙያቸው ጋር የማይገናኝ ሆኖ እያለ መስክ ለወጡባቸው በሚል አላግባብ ተከፍሎ ለግል ጥቅም የዋለ፣
- ***ግሽራቤል  ወረዳ ውሃ ሀብት ልማት ጽ/ቤት ብር 39,585.19*** በግራር አምባ ቀበሌ  የምንጭ ግንባታ ሥራ ሲከናወን የውሃ ማጠራቀሚያ ጋን ግንባታው ሳይሠራ እንደተሠራ በማስመሰል አላግባብ የተከፈለ፣
- ***ፎገራ ወረዳ ገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ጽ/ቤት ብር 26,669.24*** በሌሉና በፅ/ቤቱ በማይታወቁ ግለሰቦች ስም በተጭበረበረ መንገድ የተከፈለ ብር 16,705.00፣ በድጋሚ አላግባብ የተከፈለ ውሎ አበል ብር 3,322.40 እና  በለቀቁ መምህራን ስም ተከፍሎ የተገኘ የሚያዚያ እና ግንቦት ወር ደመወዝ ብር 6,641.84፣

- **አማራ ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት ብር 19,707.48 ከዚህ ላይ** አላግባብ በሹፌሮች ወጭ ተደርጎ ለግል ጥቅም የዋለ ነዳጅ ብር 10,307.48 እና ብር 9,400.00 ግዥ ሳይፈፀም ሃሰተኛ ሰነድ ተዘጋጅቶ ክፍያ የተፈፀመበት የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክት፣
- **አነደድ ወረዳ ዳገት ት/ቤት ብር 18,272.00** የተለያዩ እቃዎች ሲገዙ ከተከፈለው ክፍያ በላይ በወጭ ማስመስከሪያ ላይ ፊት ለፊት ቁጥር በመጨመር፣ በባዶ የወጭ ማስመስከሪያ ላይ አርሶ አደሮችን በማስፈረም ያልተቀበሉትን ገንዘብ አለአግባብ በብልጫ በማጽደቅ ለግል ጥቅም የዋለ ወጭ ፣
- **መተማ ወረዳ ኮኪት 1ኛ/ደ/ት/ቤት 12,110.00፡-ገቢው** በራሪው/ኦርጅናል/ ደረሰኝ ከተሰበሰበ በኋላ ቀሪውን ደረሰኝ ቮይድ በማድረግ ገቢ ያልሆነ ብር 300.00፣አላግባብ የተፈፀመ የጽ/መሳሪያ ወጭ ብር 835.00 ፣ያለምንም ማስረጃ የተፈጸመ የአጸደ ህጻናት ንብረት ማጓጓዣ እና የደስጣ ወረቀት ግዥ ብር 5,000.00 ፣ ለት/ቤቱ የቀድሞ ንብረት ክፍል ቋሚ ሰራተኛ ከሚከፈላቸው ደመወዝ በተጨማሪ በቤተ-መጽሀፍት አስነባቢነት ከመመሪያ ውጪ በመመደብ አላግባብ የተከፈለ ብር 5,100.00፣ ለትምህርት ጥራት ሽልማት ተከፍሏል በሚል ለግል ጥቅም የዋለ ብር 875.00 ፣
- **እንፍራንዝ ከተማ ንዑስ መዘጋጃ ቤት ብር 6,700.00 ለስራ** ከሄዱበት መ/ቤት ክፍያ ተፈጽሞ እያላ በድጋሜ የተከፈለ እና ለግል ጥቅም የዋለ የውሎ አበል እና ትራንስፖርት ወጭ፣
- **ደቡብ አቸፈር ወረዳ ውሃ ሀብት ልማት ጽ/ቤት ብር** 4,415.21 ለዋሪ አቦ ምንጭ ማጎልበት ስራ በሚል በባለሙያ የተለያዩ የውሃ ግንባታ ዕቃዎች ወጪ ሆኖ ለምንጭ ማጎልበት ስራ ሳይውል ለግል ጥቅም የዋለ፣
- **ይስማላ ጤና አጠባበቅ ጣቢያ ብር 1,330.00** የጤና አጠባበቅ ጣቢያው መፀዳጃ ቤት የጥገና ስራ ሳይከናወን ሃሰተኛ ማስረጃ ቀርቦ ለግል ጥቅም የዋለ ሂሳብ፣

በመሆኑም ድርጊቱን ከፈጸሙት ኃላፊዎች እና ሰራተኛዎች የሚፈለገው የህዝብ ሀብት ተገቢውን ክትትል በማድረግ ማስተካከትና አጥፊዎች በህግ መጠየቅ እንዳለባቸው ባሳሰብነው መሰረት ብር 90,954.81(7.05%) የተመለሰና ብር 282,327.17 በፍታብሔርና በወንጀል ክስ ሂደት ላይ ያለ መሆኑን በሪፖርት ምላሽ የተሰጠ ሲሆን ቀሪው ብር 990,747,.69 በምን ደረጃ ላይ እንዳለ አልታወቀም፡፡

### 1.8.2 ለሚመለከተዉ ፈሠስ ሳይደረግ የቀረ የተጨማሪ እሴት ታክስ፤

በ33 መ/ቤቶች ለስራ ተቋራጮች የተከፈለ የተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 6,281,536.42 በትክክል ለሚመለከተዉ ገቢ ሠብሳቢ መ/ቤት ፈሠስ ለመደረጉ ማስረጃ ሳይቀርብለት ተገኝቷል፡፡

ገንዘቡ በወቅቱ ፈሠስ መደረጉን ክትትል ባለመደረጉ ታክሱ ከመንግስት ተቋማት ተሰብስቦ ለረዥም ጊዜ በሰብሳቢዎቹ (ስራ ተቋራጮች) እጅ እየተያዘ ለስራ ማስኬጃ የሚውልበትና ከጊዜ ብዛትም ፈሰስ የማይደረግበት ሁኔታ በመኖሩ ለጉዳዩ ትኩረት በመስጠት ለግብር አስገቢው መ/ቤት ፈሰስ መደረጉ እንዲረጋገጥ ሆኖ ለወደፊቱም በክልል ደረጃ የተጀመረው የመንግስት ተቋማት ታክስን ቀንሶ የማስቀርት አሠራር እስከ ታችኛው አደረጃጀት ድረስ እንዲወርድ በሪፖርታችን ብናሳስብም የተወሰደውን እርምጃ የሚያሳይ ምላሽ አልደረሰንም፡፡

### 1.8.3. አላፅባብ □ተ□ናመ □አ□፣

ክፍያዎች በፋይናንስ ደንብና መመሪያ መሠረት የተፈፀሙ ስለመሆናቸው ሲጣራ በ114(51.58%) መ/ቤቶች የተለያየ ዕቃና አገልግሎት ግዥ ሲፈፀም በብልጫ እንዲሁም የመስክ ስራ ላላከናወኑ ሠራተኞች የተከፈለ የውሎ አበልና ሌሎች ክፍያዎች በድምሩ ብር 43,200,227.99 አላግባብ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡ዝርዝሩ እንደሚከተለው ቀርቧል፡-

***ሠንጠረዥ 9 አላፅባብ □ተ□ናመ □አ□፣***

| ተ.ቁ | አዲት ተደራጊው መ/ቤት | 2007 ሂሣብ | | | 2008 ሂሣብ | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | የመ/ቤት ብዛት | የገንዘቡ ልክ | % | የመ/ቤት ብዛት | የገንዘቡ ልክ | % |
| 1 | የክልል መ/ቤቶች | 31 | 3,526,359.35 | | 15 | 30,880,262.54 | 71.48 |
| 2 | ባሕር ዳር ከተማ | 1 | 2,320.00 | | - | - | |
| 3 | ምክ/ቶጽም | 12 | 2,028,843.00 | | 8 | 1,533,235.90 | 3.55 |
| 4 | ምስራቅ ጎጃም | 10 | 264,028.50 | | 13 | 1,762,528.26 | 4.08 |
| 5 | ሰሜን ጎንደር | 17 | 2,412,772.88 | | 5 | 747,093.82 | 1.73 |
| 6 | □ቡብ ጎንደር | 13 | 1,205,967.77 | | 11 | 1,072,772.12 | 2.48 |
| 7 | ሰሜን ወሎ | 12 | 737,820.33 | | 13 | 740,653.54 | 1.73 |
| 8 | □ቡብ □ሎ | 18 | 778,377.23 | | 15 | 3,502,014.17 | 8.11 |
| 9 | ሰሜን ሸዋ | 19 | 1,013,018.38 | | 18 | 1,463,603.53 | 3.39 |
| 10 | አዊ ብሔረሰብ | 10 | 792,013.48 | | 5 | 313,605.00 | 0.73 |
| 11 | ኻፅ□ምራብሔረሰብ | 5 | 410,106.62 | | 5 | 142,538.69 | 0.33 |
| 12 | ኦሮሞ ብሔረሰብ | 6 | 746,301.58 | | 5 | 1,041,920.42 | 2.41 |
| | ትምር | 154 | 13,917,929.12 | | 113 | 43,200,227.99 | 100 |

ከሰንጠረዡ መረዳት እንደሚቻለው በዞኖች ደረጃ አላግባብ ከተከፈለው ክፍያ ከብር 300,000.00 በላይ ድርሻ ከሚይዙት መ/ቤቶች መካከል፡-

- **ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ብር** 19,791,788.63 ለባህር ዳር ሁለገብ ስታዲዮም ግንባት ከክፍያ-2 እስከ ክፍያ ሰነድ-41 ድረስ ክፍያ ሲፈፀም በብልጫ የተከፈለ፣
- **ውሃ መስኖና ኢነርጅ ልማት ቢሮ ብር** 7,867,575.09 ቢሮው ላከናወነው የአይራራ መስኖ ልማት ፕሮጀክት የመጨረሻ ዙር ክፍያ ሲፈፀም ግንባታውን ላላከናወነ ድርጅት የተከፈለ ክፍያ፣
- **ቦረና ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር** 1,549,670.78 በመደበኛ ስራ ቦታ ላይ አላግባብ የተከፈለ ውሎ አበል፣ ከወረዳው በጀት ላይ አላግባብ ለጤና መድህን ድርጅት የተለያዩ ህትመቶች የተከፈለ፣ደጋ ዲቢ ጤና አጠባበቅ ጣቢያ ግንባታ የጨረታ ሂደት ሲፈፀም አንደኛው አሸናፊ ተጫራች እያለ ምክንያቱ ባልታወቀ ሁኔታ ሁለተኛው ተጫራጭ እንዲያሸንፍ በመደረጉ ኢኮኖሚያዊ ባልሆነ መንገድ የተፈፀመ ግዥ፣
- **አማራ ውሃ ስራዎች ኮንስትራክስን ድርጅት ብር** 997,866.75 ክፍያ ተፈጽሞ ያልቀረበ የጃክ ሀመር እና ሶስት ሊበረር ዶዘሮች ከኢፌድሪ ብረታ ብረትና ኢንጅነሪን ኮርፖራሽን ግዥ ሲፈፀም ከዶዘሮች ጋር ተገጥሞ ያልመጣ ቼን ጋርድ፣
- **ጃማ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር** 978,141.68 ለተለያዩ ሰራተኛች በስራ ገበታቸው ላይ እያሉ የተከፈለ የውሎ አበል፣ለአስተዳደር ጽ/ቤት የህንፃ ግንባታ ክፍያ ሲፈፀም ከውለታው በላይ በብልጫ የተከፈለ፣
- **ንግድ፣ኢንዱስትሪና ገበያ ልማት ቢሮ ብር** 908,910.30 ለየጁቤ ከተማ የሰሊጥ መጋዝን ግንባት2ኛ ዙር ክፍያ ሲፈጸም በብልጫ የተከፈለ፣በመደበኛ የስራ ቦታ ለተሳተፉ ሰራተኞች አላግባብ የተከፈለ የስልጠና አበል፣የኢንዱስትሪ ሸድ ግንባታ ለተከናወነበት በጎንደር ከተማ የ2ኛ እና የ3ኛ ዙር ፣በደብረ ብርሃን እና ለባህር ዳር ከተማ የ2ኛ ዙር ክፍያ ሲፈፀም ላልተሰራ ስራ የተከፈለ፣

- **ይልማና ዴንሳ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር** 807,726.98 ከጠሚት እሮብ ገበያ እና ከመሰቦ ዳባል ያለው መንገድ በ2005 ዓ.ም በሁሉን አቀፍ የገጠር መንገዶች ተደራሽነት ፕሮግራም በሊንክ ኢትዩጲያ ተቋራጭ ሲከናወን ከተያዘው ውል በላይ አላግባብ በብልጫ የተከፈለ ወጭ፣
- **መተማ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር** 543,329.44 የመኪና መለዋወጫ ዕቃ ግዥ ሲፈፀም ዝቅተኛ ዋጋ ከአቀረበው አቅራቢ መገዛት ሲገባው ከፍተኛ ዋጋ ካቀረበው አቅራቢ በመፈፀሙ ኢኮኖሚያዊ ባልሆነ መንገድ የተፈጸመ ግዥ፣ለወረዳው ሴክተር መ/ቤቶች የሚውል የቢሮ ግንባታ ሲከናወን 4ኛ፣6ኛ እና 7ኛ ዙር ክፍያ ሲፈፀም በብልጫ ተከፈለ፣
- **ደብረ ማርቆስ ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር** 488,702.23 የኮብል እስቶን መንገድ ሲሰራ ቤት ለፈረሰባቸው ግለሰቦች ክፍያ ሲፈፀም አላግባብ የተከፈለ ሂሳብ፣ከደ/ማርቆስ ኢንዱስትሪ ልማት እስከ ድብዛ ት/ቤት የተፋሰስ ጥገና ለተከናወነበት ክፍያ ሲፈፀም በብልጫ የተከፈለ፣ከአስፓልት እስከ ድንች ለተሰራው የተፋሰስ ስራ ክፍያ ሲፈፀም በብልጫ የተከፈለ፣ከአሰቡ መኖሪያ እስከ አለህኝ ታምሩ፣ከአቶ አላየሁ እስከ ዘላለም ገላው መኖሪያ ቤት እና ከሮሃ መናፈሻ እስከ ማሪያም ጻበል ድረስ ለተሰራው ኮብል ስቶን ንጣፍ ክፍያ ሲፈፀም በብልጫ የተከፈለ፣
- **እናርጅ እናውጋ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር** 459,587.39 ፍትህ ጽ/ቤት ለሚያስገነባው ህንጻ ክፍያ ሲፈፀም በብልጫ የተከፈለ፣
- **እብናት ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር** 434,555.66 ለተለያዩ ሴክተር መ/ቤት ሰራተኞች ስራ ገበታቸው ላይ እያሉ፣በድጋሚ እና አላግባብ በብልጫ የተከፈለ ውሎ አበል፣ለእብናት 2ኛ/ደ/ት/ቤት መምህራን የሰኔ ወር ደመዎዝ ሲከፈል በብልጫ የፀደቀ እና በተለያዩ ቀበሌዎች ለሴፍቲኔት ተጠቃሚዎች ክፍያ ሲፈፀም በብልጫ ተፈፀመ፣
- **ጤና ቢሮ /MDG/ ብር** 419,669.22 በቢቡኝ ወረዳ ለሚያስገነባው የመጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታል የ3ኛ ዙር ክፍያ ሲፈፀም በብልጫ የተከፈለ፣
- **ደብረ ብርሀን ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ብር** 357,752.44 የላፒደሪ ወርክ ሾፕ ግንባታ ሲከናወን ከውል በላይ አላግባብ የተፈጸመ ክፍያ፣
- **ሰከላ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር** 354,254.92 ለተለያዩ ሴክተር መ/ቤት ሰራተኞች የውሎ አበል ሲፈፀም በድጋሜ እና በብልጫ የተከፈለ፣የፍትህ ጽ/ቤት የቢሮ ግንባታ የመጀመሪያ ዙር ክፍያ ሲፈፀም በብልጫ የተከፈለ፣ለወሌማ 1ኛ/ደ/ት/ቤት የመጀመሪያ ዙር እና ለለሲማ 1ኛ ደ/ት/ቤት 2ኛ ዙር መፀዳጃ ቤት ግንባታ ክፍያ ሲፈፀም በብልጫ የተከፈለ፣
- **ማቻከል ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር** 349,741.81 ለዳጋ ሰኝ 2ኛ/ደ/ት/ቤት ግንባታ ሲከናወን የተሰጠው ቅድመ ክፍያ በተቋራጩ ስም መያዝ ሲገባው አላግባብ በግዥ ኦፊሰር ሰም የተያዘ፣ ለተለያዩ የጤና የዘመቻ ስራዎች ስራው ሳይሰራ እንደተሰራ ተቆጥሮ የተከፈለ ውሎ አበል፣
- **ዳዋ ጨፋ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር** 349,492.21 ለተለያዩ ሰራተኛቾ በድጋሜ የተከፈለ የውሎ አበል፣
- **አርጡማ ፉርሲ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር** 344,274.00 ለተለያዩ ሰራተኛች በስራ ገበታቸው ላይ እያሉ የተከፈለ የውሎ አበል ፣ለፉርሲ ሙሪ ቀበሌ የልማታዊ ሴፍቲኔት ማህበረሰብ ተጠቃሚዎች ፕሮግራም የመጋቢት ወር ደመወዝ ሲከፈል በብልጫ የተከፈለ ወጭ፣

የ2008 በጀት ዓመት አላግባብ የተከፈለ ክፍያ ከ2007 በጀት ዓመት ብር 13,917,929.12 ጋር ሲነፃፀር በመ/ቤት ቁጥር በ39 ሲቀንስ በገንዘብ መጠን ግን በብር 29,282,298.87 ጨምሮ ተገኝቷል፡፡ አላግባብ ከተፈጸመው ክፍያ ውስጥ ብር **360,501.46** (0.83%) የተተካ ሲሆን ቀሪው ገንዘብ ስለመተካቱ ይህ ጥንቅር እስከተሠራበት ሰኔ 23/2009 ዓ.ም ድረስ ለመ/ቤታችን አልተገለጸም፡፡

### 1.8.4 የግንባታ ስራዎች ወጪን በተመለከተ፤

ማንኛውም የግንባታ ክፍያ በውሉና በሥራ ዝርዝሩ መሠረት በባለሙያ እየተረጋገጠ መፈጸም ሲገባው የግንባታ ክፍያ አፈፃፀም መመሪያን ባልተከተለ መንገድ በ38(17.19%) መ/ቤቶች በድምሩ ብር 29,926,633.99 ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

ከዚህም ውስጥ ከፍተኛውን ድርሻ የያዙት መ/ቤቶች ፍኖተ ሰላም ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 9,414,905.39 ከቁራ እስከ አምሳሉ ቤት ለኮብል ስቶን መንገድ ግንባታ የጠረጋ ስራ ሳከናወነው ተቋራጭ ክፍያ ሲፈፀም የስራ ልኬት ወረቅት ሳይቀርብ የተከፈለ፣ቻግኒ ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 6,224,530.43 በከተማ አገልግሎቱ ዲሽቦይ፣አጥር፣ሽድ፣ቁራ ግንባታ ክፍያ ሲፈፀም፣ጭልጋ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 4,674,382.08 በወረዳው ትምህርት ጽ/ቤት በጫን ድባ ቀበሌ ለተገነባው ት/ቤት ግንባታ ክፍያ ሲፈፀም የሌላ የግንባታ ፕሮጀክት የስራ ልኬት ወረቀት ቀርቦ ክፍያ የተፈፀመ፣ ጓንጓ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 1,986,397.58 በብቅል እና በአሳ ብላ ወንዝ ለተገነባው የመስኖ ግንባታ ክፍያ ሲፈፀም፣ደባርቅ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 1,768,490.89 የጥራሂና ከፍተኛ 2ኛ ደ/ት/ቤት እና በአሰቦ ቀበሌ ሳለ ለማ ጎጥ ለተገነባው የውሃ ጉድጓድ ግንባታ ክፍያ ሲፈፀም ፣ፋግታ ለኮማ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 868,940.20 ፋግታ ችጓሲ እና ለበሰና ት/ቤት ግንባታ ክፍያ ሲፈፀም፣ ደጀን ወረዳነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 479,656.63 የወረዳው አስተዳደር ጽ/ቤት ላስገነባው የፍርድ ቤት ቢሮ ክፍያ ሲፈጸም፣ እብናት ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 335,335.73 እምባ ጭቆ እና የአይካና 1ኛ/ደ/ት/ቤት የተማሪዎች መፀዳጃ ቤት ግንባታ እንዲሁም የአካባቢ ጥበቃ መሬት አስተዳደር የቢሮ ግንባታ ለተሰራበት ክፍያ ሲፈጸም፣ ሊቦ ከምከም ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 379,836.98 በውሃ ጽ/ቤት በተለያዩ ቀበሌዎች ለተገነቡ የንጹህ ውሃ መጠጥ ተቋማት ክፍያ ሲፈፀም፣ ሲያ ደብርና ዋዩ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 463,659.58 ለአለም ገና የመጀመሪያ ደ/ት/ቤት የመፀዳጃ ቤት ግንባታ ሲከናወን ፣ የስራ ልኬት ወረቀት ሳይቀርብ የተከፈለ ብር 186,154.02፣በዳዋ ኮምቦልቻ ቀበሌ እነደላለ/ጽዋለ ጽድቅ ጎጥ የምንጭ ማጎልበት ግንባት ሲከናወን ብር 63,026.24፣ለጋሹ አምባ ጤና ኬላ መፀዳጃ ቤት ግንባታ ሲከናወን ብር 144,901.60፣ በአገኝ ከልበኒ ቀበሌ ቁልቋል አምባ ጎጥ የእጅ ጉድጓድ ግንባታ ሲከናወን ብር 36,006.18 እና በጨፌ አምባ ገረም ገብ ቀበሌ ማዞሪያ ጎጥ የምንጭ ማሰባሰቢያ ገንዳ ሲገነባ ብር 33,571.54፣

እነዚህ ከብር 300,00.00 በላይ ስራው ስለመከናወኑ የሚያሳዩ የስራ ልኬት ወረቀት/የክፍያ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት/ ሳይቀርብ ክፍያ ተፈፃሞ የተገኘባቸው ሲሆኑ ሥራው በትክክል ስለመሠራቱ በገለልተኛ የምህንድስና ባለሙያ እንዲረጋገጥ ሆኖ ያልተሰራ መሆኑ ከተረጋገጠ ገንዘቡ ከሚመለከታቸው ተመላሽ

እንዲደረግ እና ድርጊቱን በፈጸሙት ባለሙያዎች ላይ አስፈላጊው እርምጃ ሊወሰድ እንደሚገባዉ በኦዲት ሪፖርቶች አሳስበናል፡፡ የግንባታ ማስረጃ ሳይቀርብ ከተፈጸመው ክፍያ ውስጥ ብር 29,292.80 (0.09%) የተተካ ሲሆን ቀሪው ብር 29,897,341.19 በምን ሁኔታ ላይ እንደሚገኝ ይህ ጥንቅር እስከተሠራበት ሰኔ 23/2009 ዓ.ም ድረስ ለመ/ቤታችን አልተገለጸም፡፡

### 1.8.5 ማስረጃ ያልቀረበለት ወጪ፤

ማንኛውም □አ□ ተ□□ሞ በወጪ ከመመዝገቡ በፊት ተገቢው ማስረጃ መቅረቡ መረጋገጥ ሲገባ ይህን በመተላለፍ በ63 (28.50%) መ/ቤቶች የተለያየ የዕቃና አገልግሎት ግዥ ሲፈጸም ለተከፈለው ብር **55,161,544.30** የወጪ ደረሰኝ ወይም ፋክቱር ሳይቀርብለት □አ□ ተ□□ሞና በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡ ከዚህ ውስጥ ብር 15,292,005.38 ከኦዲት በኋላ ማስረጃ የቀረበለት ሢሆን በሪፖርት ግብረ መልስ የተገለፀ ሲሆን ቀሪው ብር 39,869,538.92 ይህ ሪፖርት እስከተጠናቀቀበት ሰኔ 23/2009 ዓ.ም ድረስ የተወሰደውን እርምጃ የሚያሳይ ግብረ መልስ አልደረሰም፡፡

ሠንጠረዥ-10 ማስረጃ ያልቀረበለት ወጪ፣

| ተ.ቁ | ኦዲት ተደራጊው መ/ቤት | 2007 ሂሣብ | | | 2008 ሂሣብ | | % |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | የመ/ቤት ብዛት | የገንዘቡ ልክ | % | የመ/ቤት ብዛት | የገንዘቡ ልክ | |
| 1 | የክልል መ/ቤቶች | 10 | 2,225,308.32 | | 5 | 24,671,616.76 | 44.73 |
| 2 | ባህር ዳር | | | | - | - | |
| 2 | ምክ/□ጸም | 7 | 1,326,397.48 | | 5 | 3,474,505.90 | 6.29 |
| 3 | ምሥ/□ጸም | 10 | 969,242.88 | | 7 | 2,127,125.70 | 3.89 |
| 4 | ሰሜን ጎንደር | 13 | 2,082,717.70 | | 5 | 4,078,686.13 | 7.38 |
| 5 | ደቡብ ጎንደር | 8 | 1,468,924.35 | | 6 | 6,428,671.10 | 11.65 |
| 6 | አዊ ብሔረሰብ | 2 | 387,614.00 | | 5 | 588,8997.40 | 10.67 |
| 7 | ሰሜን ወሎ | 5 | 4,891,274.58 | | 5 | 1,116,457.44 | 2.02 |
| 8 | □ቡብ □ሎ | 13 | 3,750,221.43 | | 11 | 1,894,998.76 | 3.44 |
| 9 | ሰሜን ሸዋ | 12 | 5,267,486.80 | | 7 | 1,045,315.39 | 1.89 |
| 10 | ኦሮሞ ብሔረሰብ | 5 | 2,130,437.40 | | 4 | 2,053,277.93 | 3.72 |
| 11 | ዋግኸምራ | 2 | 332,259.00 | | 3 | 2,381,891.79 | 4.32 |
| **ትምር** | | **87** | **24,831,883.94** | | **63** | **55,161,544.30** | **100** |

በአጠቃላይ ማስረጃ ያልቀረበለት ወጪ ካለፈው ዓመት ብር **24,831,883.94** ጋር ሲነፃፀር በ2008 በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት የተደረጉ መ/ቤቶች በቁጥር በ24 □የቀነሰ ሲሆን በገንዘብ መጠን ግን በብር 30,329,660.39 ጨምሮ ተገኝቷል፡፡ ይህም በማስረጃ አቀራረብ ዙሪያ ያለው ችግር እየተባባሰ መሄዱን ያመለክታል፡፡

ስለሆነም ክፍያን ፈፃሚውና ወጪውን የፀደቁት በ/መቤታች በከፈሉት ገንዘብ ልክ ተገቢውን ዕቃ ወይም አገልግሎት ማግኘታቸውን የማያመለክት በመሆኑ ለእያንዳንዱ ክፍያ ተገቢው ማስረጃ ቀርቦ እንዲያያዝ ወይም ያለማስረጃ የተከፈለው ገንዘብ ከሚመለከተው ላይ ተመላሽ እንዲሆን ለየመ/ቤቶች በፃፍነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

### 1.8.6. ለኦዲት ሊቀርቡ ያልቻሉ የወጪ ማስረጃዎች፣

ክፍያዎች በተገቢው ማስረጃ ተደግፈውና መ/ቤቱ ለተጠቀመበት ዕቃና አገልግሎት በትክክል ስለመዋላቸው በኦዲት ለማረጋገጥ ክፍያ የተፈጸመባቸው የወጪ ማስረጃዎች ተሟልተው ለኦዲት እንዲቀርቡ ተጠይቀው በ32 (11.94%) መ/ቤቶች ብር 124,765,448.91 የያዙት የወጪ ማስረጃዎች ለኦዲት ሊቀርቡ ያልቻሉ ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር 5,631,573.64(4.51%) ከኦዲት በኋላ ማስረጃ ቀርቦ በውስጥ ኦዲተር የተረጋገጠ መሆኑ በግብረ ተገልጿ፡፡ ቀሪው ብር 119,133,875.27 ይህ ሪፖርት እስከተጠናቀቀበት ሰኔ 23/2009 ዓ.ም ድረስ የተወሰደውን እርምጃ የሚያሳይ ምላሽ ባለመምጣቱ ግኝቱ ያለበትን ሁኔታ ማወቅ አልተቻለም፡፡ ከፍተኛ ወጪ ይዘው መረጃ ካላቀረቡት መ/ቤቶች መካከልም አርጡማ ፉርሲ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 97,081,534.73፣ባቲ ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 6,945,873.72፣ ቃሉ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 4,646,264.09፣ሞረትና ጅሩ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 2,563,760.50፣ተንታ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 2,318,469.17፣ዝቋላ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 1,758,549.13፣ ባህር ዳር ዙሪያ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 1,670,553.97፣ጣቁሳ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 1,616,277.03፣ ዋግኽምራ ብሄረሰብ ዞን ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 1,299,775.54፣ ጉባላፍቶ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 1,177,709.20፣ ዳዋ ጨፋ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 817,577.89፣ መቄት ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 481,607.85፣ ቀወት ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 429,128.15 እና ሳህላ ሰየምት ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 396,353.56 ከብር 300,000.00 በላይ የያዙ የወጪ ቫውቸሮች ከነደጋፊ ማስረጃዎቻቸው ለኦዲት ሊቀርቡ ባለመቻላቸው የወጪውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ሳይቻል ቀርቷል፡፡

ማስረጃዎቹ ምን እንደተፈፀመባቸውና ለማጭበርበር ወንጀል አለመዋላቸው ባለመረጋገጡ ስጋት ያስከተለ በመሆኑ ቀርበው የወጪው ትክክለኛነት በውስጥ ኦዲተሮች እንዲረጋገጥ ከማድረግ በተጨማሪ ሰነዶቹን የሰወሩ/ማቅረብ የነበረባቸው ሠራተኞች በህግ ተጠያቂ እንዲሆኑ በኦዲት ሪፖርቶች አሳስበናል፡፡

### 1.8.7 የግዥ ሥርዓትን ያልተከተለ የወጪ ሂሣብ፤

□ቃዎችና አገልግሎቶች ግዥ አፈፃፀም በስራ ላይ ባለ□ □ዕቃና አገልግሎት ግዥ መመሪያ መሠረት ስለመፈፀሙ እንዲሁም የተሻለ የዕቃ ጥራትና ዋጋ ለመገኘቱና የግዥ አፈፃፀም ሂደቶች የተሟሉ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በ151 (68.32%) መ/ቤቶች ብር 85,767,773.50 ዋጋ ያላቸው ግዥዎች የግዥ አፈፀፀም ሥርዓት የሚጠይቀውን መሥፈርት ሣያሟሉ ተከናውነው ተገኝተዋል፡፡ □ር□ሩም ከዚህ በሚከተለ□ ሁኔታ ቀርቧል፡፡ **ሠንጠረዥ 11 የግዥ ሥርዓትን ያልተከተለ፣**

| ተ.ቁ | ኦዲት ተደራጊው መ/ቤት | 2007 ሂሣብ | | | 2008 ሂሣብ | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | የመ/ቤት ብዛት | የገንዘቡ ልክ | % | የመ/ቤት ብዛት | የገንዘቡ ልክ | % |
| 1. | የክልል መ/ቤቶች | 38 | 13,515,315.20 | | 29 | 14,518,480.33 | 16.93 |
| 2. | ባህርዳር | | | | 1 | 175,634.00 | 0.20 |
| 3. | ምክ/□ጸም | 14 | 8,851,674.50 | | 15 | 7,574,709.52 | 8.83 |
| 4. | ምሥ/□ጸም | 17 | 12,145,339.69 | | 14 | 3,752,996.01 | 4.38 |
| 5. | ሰሜን ጎንደር | 16 | 10,897,750.69 | | 8 | 1,100,653.43 | 1.28 |
| 6. | ደቡብ ጎንደር | 12 | 21,190,741.36 | | 14 | 3,206,191.67 | 3.74 |
| 7. | አዊ ብሔረሰብ | 6 | 12,355,627.92 | | 9 | 14,069,938.52 | 16.40 |

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 8. | ሰሜን ወሎ | 12 | 6,986,735.39 | | 10 | 4,449,742.96 | 5.19 |
| 9. | □ቡብ □ሎ | 16 | 13,250,876.03 | | 15 | 2,569,901.94 | 3.00 |
| 10. | ሰሜን ሸዋ | 24 | 19,804,447.22 | | 21 | 19,412,827.28 | 22.63 |
| 11. | ኸፀ□ምራ ብሔረሰብ | 5 | 2,569,408.36 | | 7 | 10,771,330.69 | 12.56 |
| 12. | ኦሮሞ ብሔረሰብ | 6 | 5,355,726.70 | | 8 | 4,165,367.15 | 4.86 |
| | **ትምር** | 166 | 126,923,643.06 | | 151 | 85,767,773.50 | 100 |

ሠንጠረዡ እን□ሚ□መለ□ተ□ የግዥ አፈጻፀም ችግሮች ጎልቶ የሚታይባቸው መ/ቤቶች፡-

- ቻግኒ ከተማ አስ/ ነ/ፋድ/ሰ/ማዕከል ብር 9,719,123.08 ከተማ አስተዳደሩ ለሚያስገነባው የኮብል እስቶን ንጥፋ ስራ፣የዲች ግንባታ፣የኮብል እስቶን ድንጋይ ግዥ ሲፈፀም ያልግልጽ ጨረታ የተከናወነ እና የግዥ ሰራተኞች ሳያውቁት በአመራሮች ትዕዛዝ የተፈጸመ ፣ለከንቲባ ጽ/ቤት የሚውል የመኮና ጎማ እና የተለያዩ የመኪና ጌጣጌጦች፣የተለያዩ የአትክልት ዘር ግዥ ሲፈፀም ያልግልጽ ጨረታ የተከናወነ፣
- ሰቆጣ ከተማ አስ/ነ/ፋድ/ሰ/ማዕከል ብር 7,202,367.23 የግንባታ ቁሳቁስ ግዥ ሲፈፀም ንግድ ፈቃድ ከሌለው አቅራቢ የተፈፀመ ግዥ፣ የግዥ መመሪያው ከሚያዘው ውጭ የቫት ተመዝጋቢ ካልሆነ ድርጅት የተፈፀመ የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ ወጭ፣ከኮረም እስከ ስፍራ ጠራይ፣ከሆስፒታል እስከ ሁደር ወፍጮ እና መብራት ሀይል አካባቢ ለተከናወነው የኮብል እስቶን ምንጣፍ ግንባታ ለጥቃቅንና አነስተኛ ለተደራጁ ተቋማት በመመሪያ ከተፈቀደው የግዥ ጣሪያ በላይ በቀጥታ የተፈፀመ ግዥ መገኘቱ፣
- ሰሜን ሸዋ ዞን አስተዳር ነ/ፋድ/ሰ/ማዕከል ብር 5,612,897.48 የአስተዳደር ጽ/ቤት ሁለ ገብ የመሰብሰቢያ አዳራሽ የሳይት ወርክ ሾፕ ስራ ሲከናወን ያለግልጽ ጨረታ የተከናወነ፣የአማራ ብዙሃን መገኛኛ ደብረ ብርሃን ኤፍኤም የታፔላ ስራ ሲከናወን ያለግልጽ ጨረታ የተከናወነ፣
- ቴክኒክና ሙያ ኢንተርፐራይዞች ልማት ቢሮ /MDG/ ብር 3,120,542.26 በክለላ ወረዳ ላስገነባው የጀኔራል መካኒካል ወርክ ሾፕ ህንጻ ግንባታ ሲከናወን ያለግልጽ ጨረታ የተፈጸመ፣በቢሮው ስር ለሚገኙ ለተለያዩ ቴክንክና ሙያ ተቋማት አገልግሎት የሚውል የተለያዩ የማሰልጠኛ መሳሪያዎች ግዥ ተፈጽሞ የንብረት ገቢ ደረሰኝ ሳይቆረጥለት የተገኘ፣
- ጤና ጥበቃ ቢሮ ብር 2,545,220.28 ቢሮው በእንጅባራ ከተማ አንድ የመጀመሪያ ሆስፒታል ግንባታ ሲከናወን ያለግልጽ ጨረታ የተፈጸመ፣ በደጋዳሞት ወረዳ የጫት ዋርካን ጤና አጠባበቅ ጣቢያ ግንባታ ሲከናወን ያለግልጽ ጨረታ የተፈጸመ፣
- ቀወት ወረዳ ነ/ፋድ/ሰ/ማዕከል ብር 2,198,001.11 የተለያዩ የግንባታ ዕቃዎች፣የኤሌክትሮኒክስ ዕቃዎች እና ቋሚ ዕቃ ግዥ ሲከናወን ያለግልጽ ጨረታ የተከናወነ፣የግዥመጠየቂያ ሳይቀርብ የተፈፀመ የግምባታ ዕቃዎች ግዥ፣
- ሜጫ ወረዳ ነ/ፋድ/ሰ/ማዕከል ብር 2,182,686.53 ለሴክተር መ/ቤቶች የተለያዩ የጽ/መሳሪያዎች፣አላቂ እቃዎች፣የግንባታ ቁሳቁሶች ግዥ ሲፈፀም፣ለተለያዩ የወረዳው ቀበሌዎች የመንገድ ስራ ለማሰራት የግሬደርና የዶዘር ኪራይ ሲፈፀም ያልግልጽ ጨረታ የተከናወነ፣
- ሲያ ደብርና ዋዩ ወረዳ ነ/ፋድ/ሰ/ማዕከል ብር 2,162,900.63 የመኪና መለዋወጫ ዕቃ፣የውሃ ዕቃዎች፣ዴስክ ቶፐ ኮምፒውተር፣የኤሌክትሮኒክስ ጥገና፣የደን ችግኝ ዘር፣አላቂ የቢሮ ዕቃ፣የእንስሳት ህክምና የግንባታ

ዕቃዎች፣ለትምህርት ማጠናከሪያ ቁሳቁስ ግዥ፣የመምህራን እስታፍ ቢሮ ግንባታ፣የውሃ ጉድጓድ ግዥ ሲከናወን ያለግልጽ ጨረታ የተከናወነ፤ያለግዥ ጥያቄ የተፈፀመ የተሽከርካሪ ጥገና ወጭ፣

- ኤፍራታና ግድም ወረዳ ነ/ፋድ/ስ/ማዕከል ብር 1,662,962.48 ለሴክተር መ/ቤቶች የሚውል ኮምፒውተር፣ ኤሌክትሮኒክስ፣የመኪና ጎማ እና ቋሚ ዕቃዎች ግዥ ሲፈፅም ያለግልጽ ጨረታ የተፈፀመ፣
- ሚዳና ወረሞ ወረዳ ነ/ፋድ/ስ/ማዕከል ብር 1,642,815.41 የተሽከርካሪ መለዋወጫ ግዥ ሲፈፀም ያለግልጽ ጨረታ የተፈፀመ እና ዝቅተኛ ዋጋ ያቀረበ አቅራቢ እያለ መሰረታዊ ባልሆነ ምክንያት ከጨረታ ውድድር ውጭ በማድረግ ኢኮኖሚያዊ ባልሆነ መንገድ የተፈፀመ ግዥ፣
- ደብረ ብርሀን ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ብር 1,547,261.30 የተለያዩ ዕቃዎች ግዥ ሲፈፀም ያለግልጽ ጨረታ የተፈፀመ፣ ዋና ዋናዎቹና ከብር 1,500,000.00 በላይ የግዥ አፈፃፀምን ያልተከተለ ግዥዎች የተገኘባቸው መ/ቤቶች ናቸው፡፡

ግኝቱ ሊከሰት የቻለውም የግዥ መመሪያ በተገቢው መንገድ በሥራ ላይ ካለማዋል የተነሣ ገንዘቡ ተገቢዉን ዕቃ (አገልግሎት) ሳያስገኝ እና ፍትሃዊ ውድድርን ሳያስተናግድ ግዥ እየተፈፀመ እንደሆነ በማስገንዘብ ለወደፊቱ መ/ቤቶቹ ተገቢውን የእርምት እርምጃ መውሰድ እንዳለባቸው በኦዲት ሪፖርቶች አሣስበናል፡፡

የ2008 በጀት ዓመት ሂሳባቸው ኦዲት የተደረገዉ የግዥ ሂሳብ ከ2007 በጀት ዓመት ኦዲት ግኝት ብር 126,923,643.06 ጋር ሲነፃፀር በመ/ቤት ቁጥር በ15 እና በገንዘብ መጠን በብር 41,155,869.56 ቀንሶ ተገኝቷል፡፡ ይህም ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች የግዥ መመሪያውን በመከተል በኩል መጠነኛ መሻሻል መኖሩን ያመላክታል፡፡ (ዝርዝሩን አባሪ 2 ይመልከቱ)

### 1.9 . የተከፋይ ሂሳብ ኦዲት ውጤት፤

#### 1.9.1 ተቀጽላ ሌጀር ያልዘጋጀለት ተከፋይ ሂሳብ፣

የ2008 በጀት ዓመት ሂሳባቸው ኦዲት ከተደረጉት መ/ቤቶች መካከል በ43 መ/ቤቶች ብር **174,313,617.20** በመንግስት የሂሣብ አያያዝ ሥርዓት መሰረት ለማን እንደሚከፈልና መቸ እንደሚከፈል የሚያሳይ የተከፋይ ሂሣብ ተቀጽላ ሌጀር ሣይዘጋጅለት ተገኝቷል፡፡ **ሠንጠረዥ 12 ተቀጽላ ሌጀር ያልዘጋጀለት ተከፋይ ሂሳብ፣**

| ተ.ቁ. | መ/ቤት ስም | የመ/ቤቱ ብዛት | የገንዘቡ ልክ | % |
|---|---|---|---|---|
| 1 | የክልል መ/ቤቶች | 8 | 14,047,835.29 | 8.06 |
| 2 | ምዕራብ ጎጃም | 6 | 15,704,540.47 | 9.01 |
| 3 | ምስራቅ ጎጃም | 6 | 2,017,990.86 | 1.16 |
| 4 | ሰሜን ጎንደር | 2 | 5,473,347.94 | 3.14 |
| 5 | ደቡብ ጎንደር | 3 | 19,168,915.51 | 11 |
| 6 | አዊ ብሔረሰብ | 3 | 1,475,019.79 | 0.85 |
| 7 | ሰሜን ወሎ | 3 | 5,128,835.48 | 2.94 |
| 8 | ደቡብ ወሎ | 8 | 99,850,117.90 | 57.28 |
| 9 | ሰሜን ሸዋ | - | - | |
| 10 | ዋግኽምራ | 2 | 764,529.69 | 0.44 |
| 11 | ኦሮሞ ብሄረሰብ | 2 | 10,682,484.27 | 6.13 |
| | **ድምር** | **43** | **174,313,617.20** | **100** |

ከሠንጠረዡ መመልከት እንደሚቻለው የተከፋይ ሂሣብ ተቀጽላ ሌጀር አለመዘጋጀትን በተመለከተ ደቡብ ወሎ ዞን አስተዳደር (57.28%) ፣ደቡብ ጎንደር ዞን አስተዳደር(11%) ፣ምዕራብ ጎጃም ዞን አስተዳደር(9%) ፣ የክልል ተጠሪ መ/ቤቶችና ቢሮዎች (8.06%) እና ኦሮሞ ብሄረሰብ ዞን አስተዳደር(6.13%) በመያዝ በቅደም ተከተል ከፍተኛውን ድርሻ ይዘው ይገኛሉ፡፡ ተቀጽላ ሌጀር ያልተዘጋጀለትን ተከፋይ ሂሣብ በተመለከተ በጥቅሉ ስለተመዘገበ ገንዘቡ ለማንና መቸ እንደሚከፈል ገላጭ ባለመሆኑ በሥራ ላይ ያለውን የሂሣብ አያያዝ ሥርዓት በመከተል በየጊዜው ክትትል እየተደረገ በየባለቤቱ ተለይቶ መመዝገብ እንዳለበት በሪፖርታችን አስገንዝበናል፡፡

ከዚህ ተከፋይ ሂሳብ ውስጥ በግብረ መልስ እንደተረጋገጠው ብር 476,000.00 ተከፋይ ሂሳብ ተቀጽላ ሌጀር የተዘጋጀለት መሆኑ በግብረ መልስ የተገለፀ ሲሆን ቀሪው ብር 173,837,617.20 ይህ ሪፖርት እስከተጠናቀረበት ሰኔ 23/2009 ዓ.ም ድረስ የተወሰደውን እርምጃ የሚያሳይ ግብረ መልስ ባለመኖሩ ለምን ያህሉ ገንዘብ ተቀጽላ ሌጀር እንደተዘጋጀ ማወቅ አልተቻለም፡፡

## 1.10. የሂሳብ ሪፖርት ልዩነቶች፤

ኦዲት በተደረጉት መ/ቤቶች የበጀት ዓመቱ የሂሳብ ሪፖርት በትክክል የተዘጋጀ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ የሚከተሉት ልዩነቶች ተገኝተዋል፡፤ ሠንጠረዥ 13 የሂሳብ ሪፖርት ልዩነቶች፤

| በማነስ/በብልጫ | ጥሬ ገንዘብ | ባንክ ሂሳብ | የገቢ ሂሳብ | የተሰብሳቢ ሂሳብ | የወጪ ሂሳብ | የተከፋይ ሂሳብ | ዝውውር | የተጣራ ሀብት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| በማነስ | | | - | 2,348,483.51 | 517,443.03 | 531,710.07 | 5,847,386.56 | 5,847,386.56 |
| በመብለጥ | | | 184,198.28 | 416,680.00 | 2,595,232.27 | - | | |

የ2008 በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት ከተደረጉት መ/ቤቶች በአመታዊ የሂሳብ ሪፖርቶቻቸው ላይ በየሂሳብ ዓይነቱ አላግባብ በማነስና በመብለጥ ሪፖርት የተደረጉ ሂሳቦች ተገኝተዋል፡፡ ይህም የክልሉንም ሆነ የአገሪቱን የተጠቃለለ ፈንድ ሂሳብ በተገለጹት ሂሳቦች የገንዘብ መጠን በማዛባት ለውሣኔ ሰጪ አካላት የተሳሳተ መረጃ ሊሰጥ እንደሚችል ያመለክታል፡፡

ስለሆነም ማስተካከያው በየደረጃው ተደርጎ የተዛባው ሂሳብ እንዲስተካከል በየኦዲት ሪፖርቶቻችን አሳስበናል፡፡ (ዝርዝሩን አባሪ 2 ይመለከቱ)

## 1.11 የንብረት አያያዝና አጠባበቅ ኦዲት ውጤት፣

### 1.11.1 የንብረት ኦዲት ማድረግ ያልተቻለባቸው መ/ቤቶች፣

የመንግስት መ/ቤቶችና የልማት ድርጅቶች በክልሉ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 178/2003 አንቀጽ 53 እና በንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 02/2003 እና ተያያዥ የህግ ማዕቀፎች አግባብ ንብረቶች በአግባቡ ተመዝግበው፤ ክትትል እየተደረገባቸውና በየዓመቱ ቆጠራ እየተከናወነ የንብረት ሒሳብ ለኦዲት ስራ ዝግጁ መደረግ ይኖርበታል፡፡ በዚሁ መሰረት እየተሰራ መሆኑን ለማረጋገጥ በበጀት ዓመቱ በመደበኛው ኦዲት ከተደረጉት 221 መ/ቤቶች መካከል በ82(37%) መ/ቤቶች የንብረት ሂሳብን ኦዲት

ማድረግ የሚያስችል ሳይሆን ቀርቷል፡፡ ንብረትን ኦዲት አድርጎ አስተያየት መስጠት ላለመቻሉ ምክንያቶች፤

- አላቂና ቋሚ ዕቃዎች በየበጀት ዓመቱ መጨረሻ በሚገባ እየተቆጠሩ (ከFAR; UC እና BIN card) ከተመለከተው ከወጪ ቀሪ ጋር የማይመሳከሩ መሆኑ፣
- የቋሚና አላቂ ዕቃዎች መዝገብ (የእቃ መቆጣጠሪያ ካርዶች) ባለመቋቋሙ እና ቢቋቋምም ምዝገባ በተሟላ መልኩ ባለመከናወኑ፣
- የንብረት ክፍል ሰራተኞች ሲቀያየሩ የተሟላ ርክክብ የማይደረግ በመሆኑና ርክክብ ሲደረግም የርክክቡ ቀን ተገልጾ በመዛግብቶችና የንብረት ገቢና ወጪ ደረሰኞች ላይ መለያ ምልክት አለማድረግና አለመፈራረም፤
- በንብረት ግምጃ ቤት ውስጥ ንብረቶች ለቆጠራ አመቺ በሆነ መልኩ በባህሪ፤በእድሜና በአገልግሎት አይነት ለይቶ አለማስቀመጥ፣
- የንብረት ክፍል ሰራተኞች ሲቀያየሩ በቆጠራ የሚገኘውን ብቻ ቆጥሮ ለተተኪዎች ከማስረከብ ውጭ እንደመመሪያዉ ማስረከብ የሚገባቸውን ያህል ስለመሆኑ በውስጥ ኦዲተሮች በኦዲት ከተረጋገጠ በኃላ አለመሆኑ፤
- ንብረት ከመጋዝን ከወጣ በኂላም ቢሆን ሙሉ ለሙሉ ጥቅም ላይ እስኪውል ድረስ ሃብት መሆኑ ታውቆ አለመከታተል የአላቂና ቋሚ ዕቃዎች የየወሩ ከወጪ ቀሪ እየታወቀና እየተረጋገጠ በመመሪያዉ መሰረት የሒሳብ ሪፖርት አካል እንዲሆኑ አለመደረጉ የሚሉት ዋና ዋና ተጠቃሽ ምክንያቶች ናቸው፡

በመሆኑም የተጠቀሱትን የንብረት አስተዳደር መሰረታዊ ችግሮች በማረም ሊከሰት የሚችለውን የመንግስት ሃብት ብክነት እንዳይከሰት ተገቢው የንብረት አስተዳደር፤ አያያዝና አጠቃቀም መመሪያ በየመ/ቤቱ እንዲተገበርና እንዲጠናከር በየሪፖርቶቻችን አሳስበናል፡፡(ዝርዝሩን አባሪ 2 ይመልከቱ)፤

### 1.11.2 የንብረት ሂሳብ ጉድለት ብር 989,293.77፤

በንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 02/2003 እና ተያያዥ የህግ ማዕቀፎች መሰረት እየተሰራ መሆኑን ለማረጋገጥ በበጀት ዓመቱ በመደበኛና በልዩ ኦዲት ከተደረጉ መ/ቤቶች መካከል፤**በጉድለት ብር 989,293.77 መገኘቱ**፤

- **መተማ አብርሃ ጅራ ሁር ኡመር መንገድ ስራ ፕሮጀክት ብር 278,237.38** የፕሮጉክቱ ንብረት ክፍል ሰራተኛ ከየካቲት/2001 እስከ ሚያዚያ 4/2005 ዓ.ም ድረስ ያንቀሳቀሱት የንብረት ሂሳብ ተመዛዝኖ የተገኘ ጉድለት፣
- **አንዳሳ ደሮ ብዛት ማዕከል ብር 253,635.27** ከ01/04/06 እስከ 15/10/08 ዓ.ም ድረስ የንብረት ክፍል ሰራተኛው ያንቀሳቀሱት ሂሳብ ተመዛዝኖ የተገኘ የንብረት ጉድለት፣
- **ቆቦ ከተማ አስተዳደር አገልግሎት ጽ/ቤት ብር 189,662.06** የንብረት ክፍል ሰራተኛው ከ12/05/01-12/01/07 ዓ.ም ድረስ ያንቀሳቀሱት የንብረት ሂሳብ ተመዛዝኖ የተገኘ ጉድለት፣

- **ኮምቦልቻ ደሮ ብዛት ማዕከል ብር 96,849.76** የንብረት ክፍል ሰራተኛው ከ30/12/06-30/10/07 ዓ.ም ድረስ ያንቀሳቀሱት የንብረት ሂሳብ ተመዛዝኖ የተገኘ ጉድለት፣
- **ምዕራብ በለሳ ወረዳ ግብርና ጽ/ቤት 85,164.63** በንብረት ወጭ ደረሰኝ /ሞዴል 22/ ወጨ ተደርገው ለጠያቂው ያልተሰጡ /በጠያቂው ያልተወሰዱ/ንብረቶች እንደተወሰዱ ለማስመሰል አሃዝ ደልዞ በመቀየር ባልተፃፈበት መስመር ላይ ተጨማሪ ንብረት እንደወጣ በመፃፍ በተጠቃሚው ያልተወሰዱ ንብረቶችን እንደወሰዱ በማስመሰል በማጭበርበር ለግል ጥቅም የዋለ፣
- **ክልል ምክር ቤት ብር 49,772.30** ከ17/05/03 እስከ 18/10/06 ዓ.ም ድረስ የንብረት ክፍል ሰራተኛው ያንቀሳቀሱት ሂሳብ ተመዛዝኖ የተገኘ የንብረት ጉድለት፣
- **አዊ ብሄረሰብ ዞን ጤና መምሪያ** የክሊኒካል ነርስ ባለሙያው ከ1999 እስከ 2002 በጀት ዓመት ከጤና ጥበቃ መምሪያው መድሃኒቶች የዋጋ ግምታቸው ብር 35,972.37 እና ዋጋቸው የማይታወቁ በቁጥር 643 የመድኃኒትና የህክምና መገልገያ መሳሪያዎችን ወጪ አድርገው ከወሰዱ በኂላ በወቅቱ ይሰሩበት ለነበረዉ ለጃዊ ጤና አጠባበቅ ጣቢያ ገቢ ሳያደርጉ ለግል ጥቅም የዋለ፣

በመሆኑም ከንብረት ሰራተኞች የሚፈለገው ጉድለት ላይ ተገቢውን ክትትል በማድረግ ማስተካትና አጥፊዎች በህግ መጠየቅ እንዳለባቸው ባሳሰብነው መሰረት **ብር** 170,909.30 (18.90%) በፍታብሔርና በወንጀል ክስ እንዲሁም ማስረጃ በማሰባሰብ ሂደት ያለ መሆኑ ከፍትህ አካላት የተገለፀልን ሲሆን ውሳኔው እየተጠበቀ ይገኛል፡፡

## ምዕራፍ 2:- ያለፋት አምስት □መታት አፈፃፀም

### 2.1 የዕቅድ አፈፃፀም ከ2004 - 2008 በጀት ሂሳብ ዓመታት

የዋና ኦዲተር መ/ቤት በተሰጠው ተግባርና □ሃላፊነት መሠረት ካለው የሰው □ሃ□ል □ር □ተ□□መ የሥራ መርሃ ግብር በማውጣት ከ2004 □እስከ 2008 በጀት ዓመት ድረስ ያለው የ5 ዓመት ክቅት ክንውን እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡ **ሠንጠረዥ-1፡- የአምስት አመት □ክቅት ክንውን በአወቃቀር እርከን፤**

| ዓ/ም | በክልል (ማዕከል) | | በዞን | | ከተማ አስተ | | በወረዳ | | ድምር | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ዕቅድ | ክንውን | ዕቅድ | ክንውን | ዕቅድ | ክንዉን | ዕቅድ | ክንውን | ዕቅድ | ክንውን |
| 2004 | 25 | 27 | 2 | 2 | 14 | 16 | 78 | 80 | 119 | 125 |
| 2005 | 34 | 34 | 8 | 8 | 30 | 30 | 105 | 91 | 177 | 163 |
| 2006 | 187 | 165 | 3 | 3 | 32 | 32 | 169 | 168 | 391 | 368 |
| 2007 | 76 | 70 | 9 | 9 | 31 | 31 | 143 | 139 | 259 | 249 |
| 2008 | 86 | 73 | 11 | 11 | 41 | 41 | 150 | 143 | 288 | 268 |
| **ድምር** | **408** | **369** | **33** | **33** | **148** | **150** | **645** | **621** | **1234** | **1173** |

ከሠንጠረዡ መገንዘብ እንደሚቻለው የክልሉ የኦዲት ክንውን የ2004 ሂሳብ በጀት ዓመት በቁጥር የ125 መ/ቤቶች ሂሳብ ኦዲት የነበረ ሲሆን የ2008 ሂሳብ በጀት ዓመት የቅርንጫፍ ጽ/ቤቱን ጨምሮ የ268 መ/ቤቶች ሂሳብ ኦዲት ማድረግ ተችሏል፡፡ ይህም በ2008 ሂሳብ በጀት ዓመት የኦዲት ሽፋን በአሁኑ ጊዜ ካሉት 442 ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ቁጥር አንፃር ሲታይ 60.63% የደረሰ ሲሆን በ2004 በጀት ዓመት ከነበረው የኦዲት ሽፋን 114.40% ጭማሪ አሳይቷል፡፡የኦዲት ሽፋኑ ከበጀት አንጻር ሲታይ አጠቃላይ ኦዲት የተደረጉ መ/ቤቶች በጀት ለ2008 በጀት ዓመት በክልሉ ምክር ቤት ከታወጀው በጀት አንፃር ሲሰላ 86% ደርሷል፡፡

በአጠቃላይ በ5 □መታት የ1234 መ/ቤቶች ኦዲት ለማድረግ ታቅ□ 1173 /95%/ ተከናውኗል፡፡ይህም በክልሉ ከሚገኙ 442 ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ጋር ሲነፃፀር እያንዳንዱ መ/ቤት በአማካኝ በየ2.65 ዓመት የኦዲት ሽፍን ያገኙ መሆኑን ያሳያል፡፡

መ/ቤታችን የኦዲት ሽፋንን ለማሣደግ በሚያደርገው እንቅስቃሴ ከኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ብዛትና ለክልሉ ከሚመደበው በጀት አንፃር የተቻለውን ሽፋን እየሰጠ ቢሆንም የኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ቁጥር በየጊዜው በመለዋወጡና የክልሉ በጀትም ከዓመት ዓመት በመጨመሩ ምክንያት በታሰበው መሠረት በቁጥር ደረጃ ሽፋን እየተሰጠ አለመሆኑን መገንዘብ ተችሏል፡፡

ስለሆነም ጤና አጠባበቅ ጣቢያዎች፤ የአካልተሃድሶ ማዕከላት ፡ የበወረዳ የሚገኙ ፍርድ ቤቶች ፤ ማረሚያ ቤቶች ሂሣብ በየአቅራቢያቸው በሚገኝ የነጠላ ፋይናንስ ድጋፍ ሰጪ ማዕከል ተጠቃሎ የሚያዝበት ሁኔታ እንዲጠናና ተግባራዊ እንዲሆን ከዚህ በፊት የተደረሰበት ስምምነት ተግባራዊ እንዲሆን

አስተያየታችንን እያቀረብን ይህ ተግባራዊ ቢደረግ ሁሉም ኦዲት ተደራጊ ተቀማት በየበጀት ዓመቱ የኦዲት ሽፋን እንዲያገኙ ያግዛል ብለን እናምናለን፡፡

## 2.2 ከ2004 -2008 በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት የተደረጉ መ/ቤቶች ዋና ዋና የኦዲት ግኝቶች፤

ከ2004 በጀት ዓመት ሂሳብ ጀምሮ ባሉት 5 ዓመታት ኦዲት በተደረጉ መ/ቤቶች በተገኙ መረጃዎች መሠረት የዋናዋና ግኝቶች አማካይ ስሌት (Weighted-Average)ተሠርቶ የሚከተለው ውጤት ተገኝቷል፡፡

| ተ.ቁ | የኦዲት ግኝት | 2004 | 2005 | 2006 | 2007 | 2008 | ድምር | አማካኝ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የጥሬ ገንዘብ እና የንብረት ሂሳብ ጉድለት | 709,701.20 | 86,480.14 | 392,896.67 | 3,179,036.91 | 1,571,398.96 | 5,939,513.88 | 1,187,902.77 |
| 2 | የማጭበርበር ድርጊት የተፈፀመበት የገቢ ሂሣብ | 86,367.58 | 191,160.38 | 0 | 0 | 3,178,432.91 | 3,455,960.87 | 691,192.17 |
| 3 | የማጭበርበር ድርጊት የተፈፀመበት የወጭ ሂሣብ | 3,450,722.75 | 1,292,111.10 | 14,483,471.30 | 20,738,029.49 | 1,288,672.37 | 41,253,007.01 | 8,250,601.40 |
| 4 | ለግል ጥቅም የዋለ | 215,456.60 | 66,568.94 | 8,789.19 | 14,560.53 | 1,335.00 | 306,710.26 | 61,341.05 |
| 5 | አላግባብ የተከፈለ | 2,210,813.01 | 8,628,883.49 | 23,666,493.82 | 13,917,929.12 | 42,842,475.55 | 91,266,594.99 | 18,253,319.00 |
| 6 | ስርዓቱን ባልተከተለ መንገድ የተፈፀመ የግንባታ ወጪ | 41,408,198.12 | 19,007,315.58 | 21,662,955.93 | 45,059,727.70 | 29,926,633.99 | 157,064,831.32 | 31,412,966.26 |
| 7 | የግዥ ስርዓቱን ያልተከተለ | 289,013,714.62 | 107,343,734.23 | 95,503,044.01 | 126,923,643.10 | 85,767,773.50 | 704,551,909.46 | 140,910,381.90 |
| 8 | ማስረጃ ያልቀረበበት | 0 | 13,845,728.41 | 24,409,008.63 | 24,831,883.94 | 55,161,544.30 | 118,248,165.28 | 23,649,633.06 |
| 9 | ለኦዲት ሊቀርብ ያልቻለ ማስረጃ | 2,620,727.62 | 13,845,728.41 | 32,397,874.07 | 55,072,281.07 | 124,765,448.91 | 228,702,060.08 | 45,740,412.02 |
| | | 339,715,701.50 | 164,307,710.68 | 212,524,533.62 | 289,737,091.82 | 344,503,715.50 | 1,350,788,753.15 | 270,157,749.60 |


ከሰንጠረዡ መረዳት እንደሚቻለው የክልሉ የፋይናንስ አስተዳደር በተዘረዘሩት ዋና ዋና ግኝቶች ድክመት ይታይበታል፡፡ ከላይ የተመለከቱት ግኝቶች እንደየባህሪያቸው ተቀራራቢነት አጠቃላይ አቅጣጫው በሚከተሉት ግራፎች ተመልክቷል፡፡

### የጥሬ ገንዘብ ጉድለት

የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ የሚመራው በአብክመ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 178/2003፤ ደንብ ቁጥር 89/2004፤ የጥሬ ገንዘብ አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 4/2004 እና በዋና ኦዲተር መ/ቤት የፋይናንስና ህጋዊነት ኦዲት የአሰራር ማንዋሎች መሰረት ነው፡፡ ጥሬ ገንዘብ በባህሪው ለተለያዩ ብክነቶችና አደጋዎች የመጋለጥ እድሉ ሰፊ በመሆኑ በጠንካራ የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት መደገፍ ይኖርበታል፡፡ ከውስጥ ቁጥጥር ስርአቶች አፈፃፀም አንፃርም ኦዲት ሲደረግ የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ከወጪ ቀሪ ትክክለኛነት በየአመቱ

መረጋገጥ ይኖርበታል። ይህን ኦዲት ለማረጋገጥ ደግሞ የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ በመዝገብ (ሌጀር) ምዝገባ እየተካሄደ በበጀት አመቱ መጨረሻ ደግሞ በካዝና የሚገኝ ጥሬ ገንዘብና እንደ ጥሬ ገንዘብ የሚቆጠሩ ሂሳቦች የተሟላ ህጋዊ ቆጠራ መደረግና መመዛዘን ይኖርበታል። ከዚህ አንፃር መሰረታዊው ችግር ቅድመ ሁኔታዎች ስለማይሟሉ የጥሬ ገንዘብ ሂሳብን ኦዲት አድርጎ አስተያየት መስጠት የማይቻልባቸው ኦዲት ተደራጊ ተቋማት በየጊዜው ቁጥራቸው ቀላል አለመሆኑ ነው።

የጥሬ ገንዘብና የንብረት ሂሳብ ጉድለት





ከሰንጠረዡ መገንዘብ እንደሚቻለው የጥሬ ገንዘብና የንብረት ሂሳብ ጉድለት የታየባቸዉ የኦዲት ዓመቶች በ2007 ሂሳብ ብር 3,179,036.91 እና በ2008 ሂሳብ ብር 1,571,398.96 በተከታታይ ከአማካኙ ብር 1,187,902.776 በላይ በመሆን ከፍተኛውን ድርሻ ይዘው ተገኝተዋል።

በተመሳሳይ ሰንጠረዥ እንደተመለከተው በ2007 በጀት ዓመት ብር 45,023.00 የተተካ እና ቀሪዉ 670,554.48 በክስ ሂደት ላይ እንደነበር የደረሰን ምላሽ ሲያመላክት በ2008 በጀት ዓመት የተተካ ብር 25,441.67 እና ብር 218,953.72 በፍታብሄርና በወንጀል ክስ ሂደት ላይ እንዳለ በወቅቱ የደረሰን ምላሽ ያመላክታል።

**የማጭበርበር ድርጊት የተፈጸመበት የገቢ ሂሳብ**

የመንግስት ገቢ በወቅቱና በአግባቡ ተሰብስቦ ለታለመለት ዓላማ መዋል ያለበት ቢሆንም በ5 ዓመቱ ሂሳባቸው ኦዲት ከተደረጉ መ/ቤቶች ብር 3,455,960.87 በተጭበረበረ መንገድ ለግል ጥቅም ውሎ ተገኝቷል። የማጭበርበር ድርጊት የተፈጸመበት የገቢ ሂሳብ፤




ከላይ በሰንጠረዡ እንደተመለከተው በ2008 ሂሳብ ብር 3,178,432.91 በመጭበርበሩ ከአማካኝ ብር 691,192.17 በላይ በመሆን ከፍተኛውን ድርሻ ይዞ ይገኛል፡፡

በአጠቃላይ በ2008 ሂሳብ በጀት ዓመት ብር 2,977,097.74 በፍታብሔርና በወንጀል ክስ ሂደት ላይ ያለ መሆኑ የተገለፀልን ሲሆን ከሚመለከታቸው መ/ቤቶች ለማስመለስ እና ያጭበረበሩ ግለሰቦች ተጠያቂ ለማድረግ ክትትል እያደጉ እንደሆነ ከተሰጠዉ ግብረ መልስ መረዳት ተችሏል፡፡ ባለፉት ዓመታት የገቢ ሂሳብ ኦዲት ወቅት የተስተዋሉት ዋና ዋና ችግሮች የሚከተሉት ናቸው፡፡

- የካፒታል ዋጋ እድገት ስሌት ላይ ተገቢ ያልሆኑ ማስረጃዎችን መውሰድና የግብሩን መጠን በስሌት ማሳነስ፤
- የገቢ ደረሰኞችን ከ--እስከ መዝግቦ አለማሰራጨትና የተሰራጨ ደረሰኝ በትክክል ተሰርቶበት ገንዘቡ ለሚመለከተው ገቢ መደረጉ ተረጋግጦ እንዲመለስ የሚደረገው ክትትል አናሳ መሆኑ፣
- ገቢ በትክክል መሰብሰቡን ለማረጋገጥ ገቢ የተሰበሰባቸው ደረሰኞች ለኦዲት ሲፈለጉ አለመቅረብ፤
- የገቢ ደረሰኞችን አበላልጦ ገቢ መሰብሰብና ከትክክለኛው ቁጥር ላይ ስርዝ ድልዝ ማድረግ፤
- የገቢ ደረሰኞች ሲጠፉ ወደ ገንዘብ ቀይሮ ለማስከፈል በወንጀል ይጠየቁ ከማለት ዉጭ በገንዘብ ለዉጦ የፍታሐብሄር ክስ ለመመስረት የህግ ክፍተት መኖሩ፡
- የውስጥ ገቢ ያላቸው መ/ቤቶች ገቢያቸውን በዕቅድ ይዘው ለሚመለከተው አለማሳወቅና በዚያው መሠረት ስራ ላይ አውለው የሂሳብ ሪፖርት አለማዘጋጀት፣
- ገቢ ሃሳብ ሰራተኞች በስማቸው ባወጡት ደረሰኝ መሰረት ገነዘብ ከሰበሰበ በኋላ ሙሉ ለሙሉ ለሚመለከተው ዋና ገንዘብ ያዥ የባንክ አካውንት ፈሰስ ለማደረጋቸው ከስር ከስር ክትትልና ቁጥጥር አለመደረጉ የሰበሰቡትን ገቢ በእጃቸው ማቆየት ለንግድ ስራ ፣ ለብድር ወ.ዘ.ተ ማዋል/፡፡ ብሎም ለግል ጥቅም አውሎ መቅረት ፣
- ጠቃሚ የሆኑ የውስጥ ቁጥጥር ስርዓቶችን በማዳከም ለመንግስት ገንዘብ ብክነት የአሰራር ክፍተት መፍጠር፤ ለምሳሌ አንድ ሰው ደረሰኝ በስሙ ወጪ በማድረግ፤ የገቢ ደረሰኝ ራሱ በማዘጋጀት ፤ገንዘብ በመሰብሰብ፤ገቢን ራሱ መዝግቦ ለሚመለከተው ፈሰስ የማድረግ፤ በዚህ አሰራር ምክንያት ሁሉንም ስራ ደርቦ በመስራት (ቁጥጥር ሳይደረግበት) መፈፀሙ፣
- ደረሰኞችን (አንዱ ሕጋዊ ሌላው ሕገ ወጥ) ጎን ለጎን አሳትሞ በመጠቀምና ገቢ በመሰብሰብ በህገውጥ ህትመት የሰበሰቡትን ገቢ ለግል ጥቅማቸው ማዋል ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡


እነዚህንና ባጠቃላይ የገቢ አሰባሰብ በተለይም የደረሰኞችን ዝውውር (በህጋዊ ርክክብ፤ የደረሰኙን ከ---እስከ እና ሴሪ በመጥቀስ መመዝገብና ስራ ላይ የዋሉትን እየተከታተሉ ማስመለስ)፤ የገቢ አሰባሰብ ታሪፎችንና መመሪያዎችን በሚገባ ተግባራዊ በማድረግ የመንግስት ገቢን ሰብስቦ ለታቀደለት ዓላማ ለማዋል ዝግጁ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

**የማጭበርበር ተንኮል የተፈፀመበት የወጪ ሂሳብ**





ከላይ በግራፍ እንደተመለከተው የማጭበርበር ድርጊት የተፈጸመበት ክፍያ የ5 አመቱ ሲነጻጸር የ2006 በጀት ዓመት ሂሳብ ብር 14,483,471.30 እና የ2007 በጀት ዓመት ሂሳብ ብር 20,738,029.49 ከአማካዩ ብር 8,250,601.402 ከፍተኛዉን ድርሻ ይዞ ይታያል፤ ይህ የተከሰተው በአብዛኛው በላይ አርማጭሆ ወረዳ በትክል ድንጋይ መሪ መዘጋጃ ቤት፣የደብረ ብርሃን የእንጨት ማቀነባበሪያ ኃ/የተ/የግ/ማህበር፣የአብክመ ገጠር መንገዶች ባለስልጣን ከፍተኛውን ድርሻ በመያዛቸው ሲሆን ከዚህ አንፃር የ2008 በጀት ዓመት የታየው የተጭበረበረ ወጪ አነስተኛ ነው፡፡

**ለግል ጥቅም የዋለ ሂሳብ**





- ለግል ጥቅም የዋለ ሂሳብ በ2004 ብር 215,456.60 እና በ2005 ብር 66,568.94 ከአማካዩ ብር 61,341.05 በላይ በመሆነ ከፍተኛ ብልጫ አለ□፡፡ በመሆኑም በ2004 በርካታ የመንግስት ገንዘብ ለግል ጥቅም የዋለ በመሆኑ በአጥፊዎች ላይ አስተማሪ እርምጃ በመውሰድ የዉስጥ ቁጥጥር ስርዓትን ማጠናከር ያስፈልጋል፡፡

**አላግባብ የተከፈለ ክፍያ**





- አላግባብ የተከፈዉ ክፍያ በ2006 በጀት ብር 23,666,493.82 እና በ2008 በጀት ብር 43,200,227.99 ከአማካኙ ብር 18,253,319.00 በላይ በመሆኑ ከፍተኛውን ድርሻ ይዞ ይገኛል፡፡ ይህም ክፍያዎች አላግባብ የሚፈጸሙ መሆኑን ያመለክታል፡፡

**ስርዓቱን ባልተከተለ መንገድ የተፈጸመ የግንባታ ወጭ**





ስርዓቱን ባልተከተለ መንገድ የተፈጸመ የግንባታ ወጭ በ2004 በጀት ዓመት ብር 41,408,198.12 እና በ2007 በጀት ብር 45,059,727.70 ከአማካኙ ብር 31,412,966.26 በመብለጥ ከፍተኛውን ድርሻ ይዞ ይገኛል፡፡ ከዚህ እነፃር የ2008 በጀት ዓመት ብር 29,926,633.99 ከአማካኝ በታች ቢሆንም የግንባታ አፋፃፀም አሁንም አሳሳቢ ነው፡፡ **□ፅዴ ሥር□ቱን ያልጠበቀ የፅዴ**




□ፅዴ ሥር□ቱን ያልጠበቀ ፅዴ በመ□ናም በ2004 በጀት ዓመት ብር 289,013,714.62 ከአማካዩ ብር 140,910,381.9 በላይ ከፍተኛውን ድርሻ የያዘ ሲሆን በ2008 በጀት ዓመት ግኝት ከአማካኙም ሆነ ከሌሎች አመታት በታች በመሆኑ አንፃራዊ ለውጥ የታየበት መሆኑን ያሳያል፡፡

**ማስረጃ ያልቀረበለት ወጪ**




- ማስረጃ ያልቀረበለት ወጪ በ2006 ብር 24,409,008.63፣በ2007 ብር 24,831,883.94 እና የ2008 በጀት ብር 55,161,544.30 ከአማካዩ ብር 23,649,633.07 ከፍተኛ ብልጫ አለ□፡፡ በመሆኑም ከ2006 ጀምሮ በየጀት ዓመቱ የመንግስት ገንዘብ ያለበቂና አስተማማኝ ማስረጃ ክፍያ በመፈፀም በወጪ የማፅደቅ ተግባር እየተባባሰ የመጣ መሆኑን ያሳያል፡፡

**ለኦዲት ሊቀርብ ያልቻለ ማስረጃ**




ለኦዲት ሊቀርብ ያልቻለ ማስረጃ በ2007 በጀት ዓመት ብር 55,072,281.07 እና የ2008 ብር 124,765,448.91 ከአማካኙ ብር 45,740,412.02 ከፍተኛዉን ድርሻ ይዞ ይታያል፤ ይህም ማስረጃዎችን በአግባባ ይዞ ለኦዲት ስራ ሲፈለጉ በማቅረብ በኩል ከዓመት ዓመት እየባሰበት የመጣና በትክክል ለመንግስት ስራ የተፈጸሙ ክፍያዎች መሆናቸውን ለማረጋጋጥ አስቸጋሪ እንደሆነ መገንዘብ የሚያስችል ሲሆን ከዚህ አንፃር የተጠናከረ የተጠያቂነት ስርዓት ሊበጅለት እንደሚገባ ያሳያል፡፡

**በወጪ ሂሳቦች ላይ በአብዛኛው የሚስተዋሉ ዋና ዋና ግኝቶች፡**

- በክፍያና ደረሰኞች ላይ ከፊትና ከኃላ ቁጥር መጨመር፤ስርዝ ድልዝ ማድረግና ከቀረበ ማስረጃ /ደረሰኝ በላይ ሂሳብ ማወራረድ/
- በስልጠና የተሳተፉ አባላትን ዝርዝርና አቴንዳንስ፣ ሌሎች የወጪ ሰነዶችን በማዘጋጀት ክፍያ እንደተፈፀመ በማስመሰል በወጪ ማፅደቅ፤ከተለያየ ሂሳብ ላይ ለተመሳሳይ ጊዜ መክፈል፤ በስልጠና ያልተሳተፉ ሰዎች ስምን አካቶ መክፈል፤ከቦታው ታሪፍ በላይ እና በመደበኛ ስራ ላይ እያሉ ውሎ አበል መከፈል፤ የመስተንግዶ ወጪዎችን አስቀድሞ በውድድር የተመረጠ አቅራቢ አለመለየት፤ የተሳታፊዎችን ማንነትና የሚገባቸውን መስተንግዶ ዓይነትና መጠን በግልጽና ይህንኑ በሚያሳይ ውሳኔ አለማስደገፍ፤ ለብክነት በር በከፈተ አሰራር መፈፀም፣
- የግንባታ የምስክር ወረቀት ሳይቀርብ ክፍያ መፈጸም፣ በሂሳብ ስሌት ስህተት ፣ የግንባታ ስራን በትክክኛ  የክፍያ ምስክር ወረቀት ላይ አለማስቀመጥና ቀደም ባሉ ዙር ክፍያዎች የተሰራንና ክፍያ የተፈጸመበትን በድጋሚ መክፈል፤ለስራው ከተያዘው ውል በላይ ካለ ተጨማሪ ውል ክፍያ መፈጸም፤
- ተገቢውን ስፔስፊኬሽን አዘጋጅቶ ወደ ግዥ አለመግባትና የጥራት ደረጃውን ያልጠበቀ ዕቃ/ንብረት ገዝቶ ገቢ ማድረግ፤(ስፔስፊኬሽን ተዘጋጅቶ ከነበረም ከዚያ ውጭ መረከብ፤
- አስቀድሞ የተጠቃለለ የግዥ እቅድ አለማዘጋጀት እና የግልጽ ጨረታ ዘዴን የመጀመሪያ ምርጫ አለማድረግ ብሎም የግዥ ዘዴዎችን በተጨባጭ ምክንያት ላይ ተመስርቶ አለመምረጥና የግዥ ዘዴው የተመረጠበትን ምክንያት መዝግቦ/ቃለ ጉባዔ ይዞ ለ3ኛ ወገን በተጨባጭ ማስረጃነት አለማያያዝ፤
- በግልጽ ጨረታ ማስታወቂያ መገዛት ለሚገባው ግዥ የጨረታ ማስታወቂያ አለማውጣት ቢወጣም በጨረታው በቂ ተወዳደሪ እንዲቀርብ ምቹ ሁኔታ አለመፍጠር፤
- ተገቢ ማስረጃ (የግዥ ጥያቄ፤ የጨረታ ማስታወቂያ፤የተወዳደሪዎች ሰነድ፤ፕሮፎርማ፤ ቃለ ጉባዔ ውሳኔ፤ለፕሮጄክት ሥራ የክፍያ ሂሣብ ማረጋገጫ(Payment certificate) የንብረት ገቢ ደረሰኝ፤ የውል ሰነዶችን-- የመሳሰሉት) ተሟልተውና ተያይዞ ሳይቀርቡ ክፍያ መፈፀም፤
- ወጭ የተፈፀመባቸውን የወጭ ማስረጃዎች ለኦዲት ያለማቅረብ፣
- ላልተሰራ ስራ ሀሰተኛ የወጭ ማስረጃዎች በማዘጋጀት ክፍያ መፈፀም፣ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

## ምዕራፍ -3:- ማጠቃለያና የማሻሻያ አስተያየቶች፤

### 3.1 የማጠቃለያና የማሻሻያ አስተያየቶችን ከዚህ ቀጥሎ አቀርባለሁ!

**ማጠቃለያ፣**

1. በዚህ አጭር ሪፖርት የውስጥ ክፍሎች በዝርዝር እንደተመለከተው በ2008 በጀት ዓመት ሂሳቦች ላይ በተደረገው ኦዲት የግዥ ስርዓቱን ያልጠበቀ ግዥ፣ የማጭበርበር ድርጊት የተፈፀመበት የወጭ ፣ለግል ጥቅም የዋለ ሂሳብ፣ ስርዓቱን ባልተከተለ መንገድ የተፈፀመ የግንባታ ክፍያ እና የጥሬ ገንዘብ ጉድለት መጠን ካለፉት ዓመታት የተሻለ ቢሆንም የማጭበርበር ድርጊት የተፈፀመበት ገቢ፣ አላግባብ የተከፈለ ክፍያ፣ማስረጃ ያልቀረበለት ወጭ እና ለኦዲት ሊቀርብ ያልቻለ ማስረጃ የግኝቱ ሁኔታ እየጨመረ መሄዱን መረጃው ያሳያል፡፡

   በጥቅሉ ከ2004 እስከ 2008 ያሉት 5 በጀት ዓመታት ሂደቱ ሲገመገም በተወሰኑት ግኝቶች ላይ መሻሻል ቢታይም በአንዳንድ ግኝቶች ላይ እየተባባሰ መሆኑ ያመላክታል፡፡

**ጥሬ ገንዘብን በተመለከተ፤**

- የ2008 በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት ከተደረጉ መ/ቤቶች በድምሩ ብር 667,269.82 ጉድለት የተገኘ ሲሆን ከዚህ ውስጥ ከቀትሞ ገንዘብ ያገኘ ብር 414,760.32 በጉድለት ተገኝቷል፡፡
- በበጀት ዓመቱ መጨረሻ (ሰኔ 30) በጥሬ ገንዘብ ከወጪ ቀሪ መከታተያ ሌጀር መሠረት መገኘት ያለበት እና በካዝና ተገኝቶ የተቆጠረ የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ሲነጻጸር በ15 መ/ቤት ብር 4,735,882.41 የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ ውጤት ከሌጀር ከወጪ ቀሪ በማነስ (የጥሬ ገንዘብ በማነስ) እና በ2 መ/ቤት የቆጠራ ውጤት ከሌጀር ከወጪ ቀሪ በመብለጥ ብር 1,352,042.31 ተስተውሏል፡፡
- በ64 መ/ቤቶች በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ሰኔ 30/2008 ዓ.ም ላይ ያለውን የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ከወጪ ቀሪ ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለባቸው ናቸው፡፡

**የገቢ ሂሳብን በሚመለከት፤**

- የ2008 በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት ከተደረጉ 268 መ/ቤቶች ውስጥ በ69 መ/ቤቶች ብር 30,395,650.08
- ሥራ ላይ ባለው የገቢ አሰባሰብ ሥርዓት መሠረት በወቅቱ ሳ□ሰበሰብ ተገኝቷል፡፡
- ገቢ በትክክል መሰብሰቡን ለማረጋገጥ ገቢ የተሰበሰበባቸው ደረሰኞች ለኦዲት ተሟልተው እንዲቀርቡ ተጠይቀው በ62(28.059%) መ/ቤቶች ብር 18,155,823.39 የያዙ የገቢ ደረሰኞች ለኦዲት ሊቀርቡ ባለመቻላቸው የገቢውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡
- በ9 መ/ቤቶች ብር 2,916,894.29 የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ሳይቀርብ ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል

**ተሰብሳቢ ሂሳብን በሚመለከት፤**

- የ2008 በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት ከተደረጉ መ/ቤቶች ውስጥ በ117 መ/ቤቶች ብር 1,616,834,934.47 በወቅቱ በፋይናንስ የአሠራር ስርዓት መሠረት ሣይሰበሰብ (ሳይወገድ) ተገኝቷል፡፡

- የ2008 በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት ከተደረገ መ/ቤቶች ውስጥ 3 መ/ቤቶች ብር 708,125.86 ትክክለኛ ተሰብሳቢ ሂሳብ ስለመሆኑ የሚያስረዳ ሠነድ፣መቼ እንደተሰጠ፣ ከማን እንደሚሰበሰብ እና ለምን እንደተሰጠ ምንጩ ሳይታወቅ በተሰብሳቢ ሂሳብ ተይዞ ተገኝቷል፡፡
- የ2008 በጀት ዓመት ሂሳባቸው ኦዲት ከተደረጉት መ/ቤቶች መካከል በ51 መ/ቤቶች ብር **295,927,726.30** የመንግስት የሂሣብ አያያዝ ሥርዓትን በመተላለፍ የተሰብሳቢ ሂሣብ ተቀጽላ ሌጀር ሣይዘጋጅለት ተገኝቷል፡፡

## የወጪ ሂሳብን በሚመለከት፤

- በበጀት ዓመቱ ኦዲት ከተደረጉት መካከል በ15 መ/ቤቶች ብር 288,672.37 የተለያዩ የማጭበርበር ዘዴዎችን በመጠቀም ለግል ጥቅም ውሎ ተገኝቷል፡፡
- በ33 መ/ቤቶች ለስራ ተቋራጮች የተከፈለ የተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 6,281,536.42 በትክክል ለሚመለከተው ገቢ ሠብሳቢ መ/ቤት ፈሠስ ለመደረጉ ማስረጃ ሳይቀርብለት ተገኝቷል፡፡
- ክፍያዎች በፋይናንስ ደንብና መመሪያ መሠረት የተፈፀሙ ስለመሆናቸው ሲጣራ በ114(51.58%) መ/ቤቶች የተለያየ ዕቃና አገልግሎት ወጪ ሲፈፀም በብልጫ እንዲሁም የመስክ ስራ ላላከናወኑ ሠራተኞች የተከፈለ የውሎ አበልና ሌሎች ክፍያዎች በድምሩ ብር **43,200,227.55** አላግባብ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡
- ማንኛውም የግንባታ ክፍያ በውሉና በሥራ ዝርዝሩ መሠረት በባለሙያ እየተረጋገጠ መፈጸም ሲገባው የግንባታ ክፍያ መመሪያን ባልተከተለ መንገድ መጀመሪያ ከተያዘው የግንባታ ውል ጋር ባልተጣጣመ ሁኔታ በ38(17.19%)መ/ቤቶች በድምሩ ብር 29,926,633.99 ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡
- ማንኛውም □ኣ□ ተ□□ሞ በወጪ ከመመዝገቡ በፊት ተገቢው ማስረጃ መቅረቡ መረጋገጥ ሲገባ ይህን በመተላለአ በ63 (28.50%) መ/ቤቶች የተለያየ የዕቃና አገልግሎት ግዥ ሲፈጸም ለተከፈለው ብር **55,161,544.30** የወጪ ደረሰኝ ወይም ፋክቱር ሳይቀርብለት □ኣ□ ተ□□ሞና ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡
- ክፍያዎች በተገቢው ማስረጃ ተደግፈውና መ/ቤቱ ለተጠቀመበት ዕቃና አገልግሎት በትክክል ስለመዋላቸው በኦዲት ለማረጋገጥ ክፍያ የተፈጸመባቸው የወጪ ማስረጃዎች ተሟልተው ለኦዲት እንዲቀርቡ ተጠይቀው በ32 (11.94%) መ/ቤቶች ብር 124,765,448.91 ስለ ክፍያው ትክክለኛነት የሚያስረዳ ደጋፊ ማስረጃ ሳይቀርብለት ሂሳቡ በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡
- የዕቃዎች አገልግሎቶች የግዥ ስርዓቱን ያልጠበቀ በ151 መ/ቤቶች ብር 85,767,773.50 ዋጋ ያላቸው ግዥዎች የግዥ ስርዓትን የሚጠይቀውን መስፈርት ሳያሟሉ ተከናውነው ተገኝተዋል፡፡

## የንብረት አያያዝ፤ አጠባበቅና አጠቃቀምን በተመለከተ፤

በበጀት ዓመቱ በመደበኛው ኦዲት ከተደረጉት 221 መ/ቤቶች መካከል በ82(37%) መ/ቤቶች የንብረት ኦዲት ማድረግ ሳይቻል ቀርቷል፡፡

በንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 02/2003 እና ተያያዥ የህግ ማዕቀፎች መሰረት እየተሰራ መሆኑን ለማረጋገጥ በበጀት ዓመቱ በመደበኛና በልዩ ኦዲት ከተደረጉ መ/ቤቶች መካከል፤በጉድለት ብር 989,293.77 መገኘቱ በኦዲት ተረጋግጧል፤

**የማሻሻያ አስተያየት፤**

በ2008 በጀት ዓመት የኦዲት ሪፖርቶች ከተስተዋሉ ግኝቶችና ከላይ ከተሰጠው ማጠቃለያ ከክልል እስከ ወረዳ ባሉ የመንግስት መ/ቤቶች የፋይናንስና ሌሎች ሀብቶችን አመራር ለማጠናከር የሚከተሉትን የማሻሻያ አስተያየቶችን እናቀርባለን፣

**በጥሬ ገንዘብ ሂሳብ አያያዝ ሥርዓት ላይ ቁጥጥሩን ማጠናከር ስለማስፈለጉ፤**

በኦዲት ስራው ከተስተዋሉ ግኝቶች መረዳት እንደተቻለው በአብዛኞቹ መ/ቤቶች የጥሬ ገንዘብ ሂሣብ በተለያዩ ምክንያቶች ማመዛዘን ያልተቻለ ሲሆን ይህም የመንግስትን ገንዘብ ለብክነትና ለምዝበራ የሚዳርግ በመሆኑ በየመ/ቤቱ የሚገኙ ሥራ አመራሮችና የውስጥ ኦዲተሮች ለጉዳዩ ትኩረት ሊሰጡት ይገባል፡፡

**የወጪ ሂሳብ ማጭበርበሪያ ክፍተቶችን በአሠራር ስርዓት ስለመዘርጋት፤**

በወጪ ሂሣብ ላይ ለተከሰቱ የማጭበርበር ድርጊቶች ክፍተት የፈጠሩ አሠራሮችን እየፈተሹ በመድፈንና የፈጻሚዎችንና አመራሮችን አቅም በመገንባት የመንግስት ሃብትን በአግባቡ ይዞ መጠቀም እንዲቻል ማድረግና የፍትህ አካላትም በአጥፊዎች ላይ ተገቢ የሆነ እርምጃ ሊወስዱ ይገባል እንላለን፡፡

**የቋሚና አላቂ ዕቃዎች አያያዝና አጠባበቅ መጠናከር የሚገባው ስለመሆኑ፤**

በአብዛኞቹ መ/ቤቶች የቋሚና አላቂ ዕቃዎች መዝገብ ተቋቁሞ የማይሠራባቸውና በየበጀት ዓመቱ መጨረሻ ቆጠራ የማይከናወን በመሆኑ የንብረት አያያዝና አጠባበቅን ኦዲት አድርጐ አስተያየት መስጠት ያልተቻለ ስለሆነ መ/ቤቱቹ ለቋሚና አላቂ ዕቃዎች መዝገብ በማቋቋምና በየጊዜው ቆጠራ እያከናወኑ ከመዝገብ ከወጪ ቀሪው ጋር እያመሳከሩ ልዩነት ሲፈጠርም ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ እየወሰዱ ሊሰሩ የሚገባ ሲሆን ይህን ተግባራዊ በማያደርጉ የየተቋሙ ሃላፊዎችና ሰራተኞች ስራን ባልተመቸ ሁኔታ መምራትና ለብክነት በር በመክፈት ወንጀል ሊጠየቁ ይገባል፡፡

**በየደረጃው ያሉ የህዝብ ምክር ቤቶች በኦዲት ሪፖርት ላይ ክትትል ሊያደርጉ ያስፈልጋል፡፡**

በየደረጃው የሚገኙ ም/ቤቶች ለየአካባቢያቸው በሚደርሰው የውጪ እና የውስጥ ኦዲት ሪፖርቶች በክልሉ ም/ቤት እንደሚደረገው ሁሉ በበጀትና የመንግስት ፋይናንስ ጉዳዩች ቋሚ ኮሚቴ አማካኝነት ለየም/ቤቱ ጉባኤ በአጀንዳነት ቀርቦ ውይይት ሊደረግበትና አቅጣጫ እየተሰጠበት ክትትሉ ሊጠናከር ይገባል እንላለን፡፡

በሌላ በኩል ባለፈው ዓመትም ቀርቦ መፍትሔ ያላገኘውን ልማቱ የፈጠራቸው አዳዲስ መ/ቤቶችን በተመለከተ፤ መ/ቤታችን የኦዲት ሽፋንን ለማሣደግ በሚያደርገው እንቅስቃሴ ከኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ብዛትና ለክልሉ ከሚመደበው በጀት አንፃር የተቻለውን ሽፋን እየሰጠ ቢሆንም የኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ቁጥር በየጊዜው በመጨመሩ ምክንያት በታሰበው መሠረት በቁጥር ደረጃ ሽፋን እየተሰጠ አለመሆኑን መገንዘብ ተችሏል፡፡

ለዚህም ምክንያቱ በጀታቸው በተነጻጻሪ ደረጃ አነሰተኛ ቢሆንም እንደ ጤና አጠባበቅ ጣቢያዎችና የወረዳ ፍርድ ቤቶች ያሉ መ/ቤቶች ሂሣባቸውን ራሳቸውን ችለው ስለሚያንቀሳቅሱና እንደ አንድ ኦዲት ተደራጊ መ/ቤት ስለሚቆጠሩ የኦዲት ተደራጊውን መ/ቤት ቁጥር እየጨመሩት ይገኛሉ፡፡ በመሆኑም ከዚህ በፊት በተደጋጋሚ

ያቀረብነው የመፍትሄ ሂሳብ በጥናት ተደግፎና በአቻ ክልሎች ካለው አሰራር ጋር ተቃኝቶ ውሳኔ ሊያገኝ እንደሚገባ አስተያየታችንን እናቀርባለን፡፡

በመጨረሻም የተከበራችሁ የምክር ቤት አባላት፣የምክር ቤቱ አፈ ጉባኤዎች፣የበጀትና የመንግስት ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴና ሌሎች ኮሚቴዎች፣የፍትህ አካላትና ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች በሥራ ሂደት ላደረጋችሁልን የስራ ትብብር እና የመ/ቤቱ ሠራተኞች ደግሞ በዚህ ሪፖርት ለተገኙት ውጤቶች ላሳዩት ታታሪነትና ላላቸው መልካም ስነ-ምግባር ከፍተኛ ምስጋና እያቀርብኩ ሪፖርቴን በዚሁ አጠቃልላለሁ፡፡ አመስግናለሁ!!

ስመኝ ካሴ እንደሻው

ምክትል ዋና ኦዲተር

ሐምሌ/2009